# የቤ/ጉ/ክልል መንግስት የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ

## የሁለት ዓመት የልማት ዕቅድ

(2016-2017)

ነሐሴ /2015

አሶሳ

## የአርዕስት መግለጫ ገጽ


1. መግቢያ ........ 3
2. ዓላማ ........ 3
3. የጥናቱ ወሰን ........ 4
4. የጥናቱ ስልት ........ 4
5. የሚጠበቅ ውጤት ........ 4
6. ተቋማዊ ዳሰሳ ........ 5
6.1. ሀገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፤ ........ 5
6.1.1. የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ትንተና ........ 5
6.1.2. የኢንቨስትመንት ዘርፍ ፖሊሲ ትንተና ........ 7
6.2. የባለድርሻ አካላትና የተገልጋዮች ፍላጎት ትንተና ........ 8
6.3. የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ ትንተና ........ 15
6.4. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ትንተና ........ 19
6.5. ትኩረት የሚሹ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ........ 20
7. የቢሮዉ ተልዕኮ፣ራዕይ እና እሴቶች ........ 20
7.1. ተልዕኮ /Mission/ ........ 20
7.2. ራዕይ /vision/፣ ........ 20
7.3. እሴት /values/ ........ 20
8. ለተቋሙ በአዋጅ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ........ 21
ደረጃ ሁለት ........ 23
2. ስትራቴጅያዊ የትኩረትመስኮች፣ውጤቶች እና እይታዎች ........ 23
2.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች ........ 23
2.2. የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች መግለጫ ........ 24
2.3. የትኩረት መስኮች እይታዎች ........ 26
ደረጃ ሶስት ........ 28
**3. ስትራቴጂያዊ ግቦች** ........ 28
3.1. የትኩረት መስክ እና ስትራቴጂያዊ ግቦች ........ 28
3.2. የቢሮ የተጠቃለለ ስትራቴጂያዊ ግቦች መግለጭያ ........ 31
3.3. የቢሮ የተጠቃለለ ስትራቴጂያዊ ግቦች ........ 35
ደረጃ አራት ........ 36
4. ስትራቴጂያዊ ማፕ ........ 36

4.1. የተቋሙ የተጠቃለሉ ስትራቴጂያዊ ግቦች ..... 38
ደረጃ አምስት ..... 39
5. ስትራቴጂያዊ መለኪያዎችና ዒላማዎች ..... 39
5.1. ስትራቴጂያዊ መለኪያዎች ..... 39
5.2. ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ መለኪያዎች እና ዒላማዎች የሁለት ዓመት ተደራሽ ..... 42
5.3. የግብ ማሳኪያ ዋና ዋና ተግባራት (2016-2017) ..... 44
5.4. ተቋማዊ ዒላማዎች መግለጫ እና የአፈፃፀም ደረጃ መነሻ ሀሳብ ..... 47

## 1. መግቢያ

በ2022 ኢትዮጵያ፤‹‹አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት››ለማድረግ ሀገራዊ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ እንደ ሀገር ይህን የልማት ጉዞ በስኬት ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችም ተነድፈው ለልማትና ዕድገት አመቺ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የተደረገ ሲሆን ሌሎች በቀጣይ ተግባራዊ የሚደረጉ የኢንዱስትሪና የኢንቨስትምት ፖሊሲና ሌሎች አዳዲስ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመጨመር በዘርፉ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ከዚህ ቀደም በመሬት አስተዳርና ኢንቨስትምት ቢሮ እንዲሁም በክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ አገልግሎቱ ሲሰጥ የቆየ ሲሆን መንግስት አገግሎት አሰጣቱን ለማሳለጥ በማሰብ አደረጃጀቱን ለማሻሻል በወጣው በአዋጅ ቁጥር 197/2015 መሰረት በአዲስ ተቋቁሟል፡፡ ከዚህ ቀደም በነበረበት አደረጃት በሁለቱም ዘርፎች ያለውን የሀብት አማራጮች በማጥናት እና በማስተዋወቅ ልማታዊ ባለሃብቶች እንዲመጡ በማድረግ ያላቸውን ገንዘብና እውቀት በክልሉ ላይ እንዲያውሉ በማድረግ የክልሉን የገቢ አቅም በማሳደግ፣ ለህ/ሰቡ የስራ እድል በመፍጠር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማስፋፋትና በማስተላለፍ፣ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ ጉልህ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ስለሆነም ቢሮው የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት ያስችለው ዘንድና ሀገሪቱ የነደፈችውን የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ለማስፈጸም የሚያስችል ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በዚሁም መሰረት ቢሮው ከተዋቀረበት ዓላማ አንፃር የቀሪ ሁለት ዓመት ሊያሰራ የሚችል ስትራቴጂክ እቅድ ለማዘጋጀት የኢንዱስትሪና የኢንቨስትመንት የህግ ማዕቀፎች፣ ሀገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመፈተሽ፣ የክልሉን ወቅታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በመንተራስ፤ የክልሉን ነባራዊ ሁኔታዎችን በዝርዝር በመዳሰስ፤ የአጋርና ተባባሪ አካላትን አስተያየት እንደ ግብዓትነት በመጠቀም የቢሮውን እስትራቴጂክ የቀሪ ዘመን እቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ይህንን መሪ እቅድ መሰረት በማድረግ በሴክተሩ የሚገኙ ሁሉም ተቋማትን በማጠናከር፣ በማቀናጀትና በማስተባበር ወቅቱ የሚፈልገውን ልማትና አገልግሎት ለማቅረብ እንዲቻል የ10 ዓመቱን መሪ እቅድ መነሻ በማድረግ የሁለት ዓመታት (ከ2016-2017) ዓ/ም ድረስ የሚተገበር እቅድ በዉጤት ተኮር ስርዓት ተዘጋጅቶ እየተተገበረ የሚገኝ ሲሆን የቢሮው የሁለት ዓመት ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. ዓላማ

የዕቅዱ ዋነኛ አላማ በቀጣይ ሁለት ዓመታት (ከ2016-2017) የሚያገለግል ዕቅድ በማዘጋጀት "በ2022 ፍትሀዊ እና ተወዳዳሪ የሆነ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተስፋፍቶ ማየት" በሚለው

የተያዘውን ተቋማዊ ራዕይ ከማሳካት አንጻር የሴክተሩን ተልዕኮ የማስፈጸሚያ ዋናዋና አቅጣጫዎችን ለማመላከት እና የዕለት ተዕለት አተገባበራቸውን ለመከታተልና ውጤታማነታቸውንም ለመመዘን የሚያስችል የውጤት ተኮር ስርዓት በማዘጋጀትና በየደረጃው ለሚገኙ ባለድርሻ አካላት በማውረድ ውጤታማ የሥራ አመራር እና የመለኪያ ስርዓት መዘርጋት ነው ፡፡

## 3. የጥናቱ ወሰን

?? ???? ??? ??? ?????? ??? ???? ? ? ? ?? ???? ?????? ?? ????? ???? ??? ?? ? ?? ???? ?????

## 4. የጥናቱ ስልት

- ከውጤት ተኮር ሥርዓት ስልጠና የተገኘን ዕውቀት እና የተለያዩ ፅሁፎችን በመጠቀም፣
- ከማኔጀመንት እና ከሠራተኛው የሚሰጡ አስተያየቶችና አቅጣጫዎችን በመጠቀም፣
- በውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅት ወቅት የተገኙ ጥሩ ተሞክሮዎችን በመጠቀም፣
- ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተገኘ ልምድን ቀምሮ በመጠቀም፣
- የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሰነድ በመዳሰስ፣
- የግምገማ ዉጤቶችና ተሞክሮዎችን በመጠቀም፣
- የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት በማየት፣
- የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣
- የስትራቴጂክ ዘመኑ የግማሽ ዓመት አፈፃፀም
- የወጡ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣

5. የሚጠበቅ ውጤት

የቢሮውን የቀሪ ዘመን የሁለት ዓመት ዕቅድ በማዘጋጀት በየደረጃው ላሉ ባለድርሻ አካላት በማውረድ የስራ አመራር ስርዓት መዘርጋት ሲሆን በዚህ ሂደትም፡-

- በቢሮው የተመረጠውን የትኩረት መስክና የተጣሉትን ስትራቴጂያዊ ግቦች በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላት በኃላፊነት ወስደዉ በባለቤትነት እንዲሰራና ለሚመዘገበው ውጤት ተሸላሚና ተጠያቂ እንዲሆን ማስቻል፣
- በሁሉም ደረጃ የተቀናጀ የፕሮግራም ትግበራን እውን ለማድረግ የሁሉም ፈጻሚ አካል አስተዋጽኦ አስፈላጊ በመሆኑ ተሳትፎአዊ አሠራርን ለማስፈን፣

- በደራሽ ሥራዎች የመጠመድን ችግር ለማስወገድና ስትራቴጂያዊ በሆነ አስተሳሰብ የዕቅድ አፈጻጸምን ለመምራትና ለእርምት እርምጃ አወሳሰድ ምቹ ሁኔታ ለመፈጠር ነው፡፡

6. ተቋማዊ ዳሰሳ

## 6.1. ሀገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፤

ቀጣይነት ላለዉ የኢኮኖሚያዊ እድገት አንዱ ምሰሶ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት በመሆኑ የዘርፎቹ መስፋፋት ለዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር፣ የገቢ ግኝት በማሳዳግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን፣ ተኪ ምርትን ማሳደግ እና በአጠቃላይ የክልሉን ምርትና አገልግሎትን በማስፋት የክልሉን ኢኮኖኒያዊና ማህበራዊ እድገት መፋጠን ጉልህ አስተዋጾ ለማድረግ ነዉ፡፡ ይህም በመሆኑ ለሀገሪቱ ራዕይ እዉን መሆን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ መንግስት ሀገሪቷን በ2022 አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት በማድረግ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች አንዷ ለማድረግ ያስቀመጠውን ራእይ እውን እንዲሆን የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በማዉጣት ተግባራዊ በማድረግ ይገኛል፡፡

የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር በዚህ ዙሪያ ከወዲሁ በቂ ግንዛቤ ሊኖር ይገባል፡፡ ከኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ላላቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ሃገሪቱ ነድፋ ካስቀመጠቻቸዉ ግንባር ቀደም ስትራቴጂዎች መካከል ከዚህ በታች የተቀመጡትን በዝርዝር ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

### 6.1.1. የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ትንተና

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በባህሪው ከሌሎች ዘርፎች በተሻለ የእርስ በእርስ ትሥሥር የሚስተዋልበት፣ የባለድርሻ አካላትን ርብርብን የሚጠይቅ፤ የፊትዮሽና የኋልዮሽ ትሥሥር የመፍጠር አቅም ያለው ዘርፍ በመሆኑ የዘርፉ መጠናከር እና መጎልበት በርካታ የስራ እድሎችን እንዲፈጠሩ ምክንያት በመሆን ስራ አጥነትን ለመቀነስ እና መዋቅራዊ ሽግግር ለማድረግ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ከዚህም ባለፈ የውጭ ምንዛሬን በማመንጨት እና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሬን በመቆጠብ የተሻለ የንግድ ሚዛን መመጣጠን እንዲኖር ያስችላል። የዘርፉ መስፋፋትና መጠናከር በኢኮኖሚው ውስጥ የመዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ በማስቻል ለሌሎች ዘርፎች መዘመን ምክንያት በመሆን በአንድ ሀገር የልማት ሂደት ውስጥ እንደ ጀርባ አጥንት ሆኖ ያገለግላል።

በኢትዮጵያ ባለፉት አመታት ፈጣን የሚባል የኢኮኖሚ እድገት ቢኖርም የአምራች ኢንዱስትሪው ከክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ 0.81 በመቶ ያልበለጠ ነበር፡፡ ዘርፉ በአጠቃላይ ሲቃኝ በጎጆ ኢንዱስትሪዎች የተዋጠ ከመሆኑም በተጨማሪ አዝጋሚ ለውጥ የታየበት ዘርፍ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው በ2010 በተጠናዉ በክልላዊ ገቢ አጥኚ ቡድን ባጠናዉ ጥናት መሰረት ከጠቅላላ የአምራች ኢንዱስትሪ ድርሻ 0.79 በጎጆ ኢንዱስትሪ የመጣ ነበር፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛና በትላልቅ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ 40 በመቶ የሚሆነው የተገኘው ከዚሁ ዘርፍ ነው፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ላይ ጥገኛ በመሆኑ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ያለው ተፅዕኖ እና ፋይዳ ደካማ ነው፡፡ ለምሳሌ ከአጠቃላይ የማምረቻ ወጪዎች ውስጥ ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶች ድርሻ ለማሽነሪ ዘርፍ (machinery and equipment) 93.3 በመቶ ሲሆን ለብረታ ብረት ዘርፍ ደግሞ (iron and steel) 79 በመቶ ይደርሳል፡፡ በተመሳሳይ የጨርቃጨርቅና አልባሳት እንዲሁም የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፎች ከውጭ በሚመጡ ግብዓቶች ላይ ጥገኛ ናቸው፡፡ ከቆዳ እና ከጨርቃጨርቅ ዘርፎች ውጭ ያሉ የአምራች ዘርፎች ከሚያመርቱት ምርት ውስጥ ለውጭ ገበያ ማቅረብ የቻሉት ከ2 በመቶ በታች ነው፡፡ በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪው የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻም ከ30 በመቶ ያልበለጠ ነዉ፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪው የማምረት አቅም በውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ላይ የተመረኮዘ መሆኑ፤ ያሉት አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሌሎች ላዕላይ ኢንዱስትሪዎች (upstream industries) ጋር ያላቸው ቁርኝት ዝቅተኛ መሆኑ፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት መጓደል በተለይም የኃይል አቅርቦት፣ ብቁ የሰለጠነ የሰው ሀይል አለመኖር፣ የተንዛዛና ገዳቢ የመንግስት ቢሮክራሲ እና ከግሉ ዘርፍ አቅም ውስንነት ጋር ተደምሮ የዘርፉን የማምረት አቅም ከ50 በመቶ በታች አድርጎታል፡፡ በተመሳሳይ የአገልግሎት እና ተያያዥ ዘርፎች (non-tradable sectors) ትርፋማ መሆናቸውና በአንጻራዊ መልኩ አነስተኛ ስጋት (risk) ስላላቸው የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ያለው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ መሠረታዊው ችግር ዘርፉ ለአገራችን የረጅም ጊዜ ባህል ባለመሆኑ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶቻችንን ‹የኢንዳስትሪያሊስትነት› ደረጃ ለማድረስ ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል፤ ለዚህም የቴክኖሎጂ ሽግግር ወሳኝ ነው፡፡

ሀገራችን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር የመዋቅራዊ ሽግግር ለማድረግ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና እቅዶችን በማዘጋጀት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ባለፉት ዓመታትም ይህን መዋቅራዊ ሽግግር እዉን ለማድረግ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም የሚፈለገዉ ለዉጥ ግን ሊመጣ

አልቻለም፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ሁለት ዓመት ውስጥ የተጀመረዉን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለሚደረገዉ መዋቅራዊ ሽግግር በትኩረትና በላቀ ደረጃ መፈጸም ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ በክልላችን ያለፉ አመታት የኢንዱስትሪዉ ዘርፍ አፈጻጸም ሲገመገም በጅምር ላይ ያለ በመሆኑ የኢኮኖሚ መዋቅር ሽግግር ለማምጣትና መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ የኢንዱስትሪ ዘርፍ በዕቅድ ዘመኑ በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚናን መጫወት የሚችልበት ደረጃ ላይ ለማድረስ፣ ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሃዊ ኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት የተረጋገጠበት የኢንዱስትሪ ልማት በማስፈን ዘርፉ ቀስ በቀስ ኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚና እንዲጫወት ማድረግ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በቀጣይነት ለማሳካት በዘርፉ የሚታዩ የቴክኖሎጂ አቅም መዋቅራዊ አደረጃጀት ችግሮችን መፍታት፤ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መስራት፤ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ፤ ገበያ ማስፋፋት፣ የግብዓትና ጥሬ ምርት አቅርቦት ማሳደግ፣ የማምረቻ ቦታ እና የመሸጫ ቦታዎችን ምቹ በማድረግ እና የካፒታል ሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የኢንዱስትሪዎችን ዕድገት በመደገፍ የኢኮኖሚ መዋቅር ሽግግር ለማምጣት ኢንዱስትሪ ልማት የወደፊት የልማታችን ወሳኝ በመሆኑ በቀጣይ ሁለት ዓመት በትኩረት መስራትን ይጠይቃል፡፡

### 6.1.2. የኢንቨስትመንት ዘርፍ ፖሊሲ ትንተና

በኢንቨስትምንት ዘርፍ ለሚሰማሩ የልማታዊ ባሀብቶች የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠር በክልሉ ውስጥ ያለውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማነቃቃት ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍ ያለ እንደሆነ ይታመናል ቀጣይ የኢንቨስትመንት ልማቱን ለማረጋገጥ እንዲቻል የዋጋ ግሽበትን፣ የወለድ መጠንና የውጭ ምንዛሪ ተመንን በፊስካል ፖሊሲና በሌሎች ዘዴዎች በማስተካከል የተረጋጋና ለልማት የሚያመች የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን የመፍጠር አሰፈላጊነት፣ የባንኮችንና ባንክ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋሞች ፣የገጠር የፋይናንስ ተቋሞችን አሰራር በማሻሻልና በማስፋፋት ዘመናዊና ለልማት የተመቻቸ የፋይናንስ ሥርዓት መፈጠሩ ኢንቨስትመንትና ልማትን የሚያፋጥን መሆኑንና የመንገድ ፣የቴሌኮሙንኬሽን ፣የኤሌክትሪክ ኃይል ፣ የውኃና የመሬት የቅርቦትን በማጠናከርና በማስፋፋት አስተማማኝ የኢንቨስትምነት እንቅስቃሴ እንዲኖር በማስቻል አገልግሎቶችን ማቅረቡ የስትራቴጂዉን አፈፃፀም እንድያፋጥን ያደርጋል፡፡

በኢንቨስትመንቱ ልማት ስትራቴጂው ለሁሉም የልማት መስኮች የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር እንደተጠበቀ ሆኖ ሀገሪቷ ካላት አቅም የተለየ ድጋፍ የሚደረግላቸው የልማት መስኮች በዋናነት የጨርቃ ጨርቅና የልብስ ስፌት፣ የሥጋ፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ፣ የአግሮ ፕሮሰሲንግ

ኢንዱስትሪ አነስተኛና ጥቃቅን ኩባንያዎች እና ቱሪዝም የመሳሰሉት መኖራቸዉ በተመሣሣይ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ በተለይ ገጠርን ማዕከል ያደረገ የግብርና ልማት ስትራቴጂ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ዕሙን ነው፡፡

ይህም ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ መሬት ከፍተኛ የሰው ጉልበትንና ውስን ካፒታልን በመጠቀም ብዙሃኑን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መኖሩ፣ ለአገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት የላቀ ድርሻ ያለውን የግብርና ዘርፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለዉ ዕድገትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል በዚሁ መሰረት የስትራቴጂው መሠረታዊና ዋነኛ ጉዳዮች ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት በማካሄድ ፈጣን ዕድገትን በማረጋገጥ፣ ሕዝቡን ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ፣ ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት ላይ በመመሥረት በአገራችን የዳበረ ነጻ የገበያ ኢኮኖሚ መፍጠር፣ እና በኮሜርሻል ግበርና ላይ የግሉ ባለሀብት እንዲሳተፍ ማድረግ ናቸው፡፡

ስለሆነም ከግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲ አቅጣጫ  መካከል አንዱ የሆነው የግል ባላሃብቶች በግብርና ልማት ዘርፍ የሚኖራቸውን ደርሻ ከፍ እንዲል በማድረግ አገሪቱን ከድህነት ማውጣት ነው፡፡ በተጨማሪም የግብርናው ዘርፍ ቀጣይነት ያለው የምርት ዕድገት ካስመዘገበ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት እንዲኖረው መሪ ሚና ይጫወታል፡፡

## 6.2. የባለድርሻ አካላትና የተገልጋዮች  ፍላጎት ትንተና

የባለድርሻ አካላትና የተገልጋዮች የተፅዕኖ ደረጃ መለየት ለስትራቴጂ ዝግጅት አስፈላጊ በመሆኑ የተፅዕኖ ደረጃቸዉን ለመለየት የሚከተሉትን ዋና ዋና መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የተቋሙ፣ የባለድርሻ አካላትና የተገልጋዮች የተፅእኖ ደረጃ ተለይቷል፡፡

- በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ካላቸው ተፅዕኖ አንፃር፣
- በበጀት/ገቢ ላይ ያላቸዉ ተፅዕኖ ደረጃ፤
- ተቋሙ የሚሰጣቸዉ አገልግሎቶችና ድጋፎችን በአብዛኛዉ የሚጠቀሙ መሆኑ፤
- ከመንግስት የለውጥ ትኩረት አቅጣጫ አንፃር፣
- የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት ካላቸው ሚና፣
- ባለድርሻ አካላት ከተቋሙ የሚፈልጓቸዉ አገልግሎቶች፣
- የሚፈልጉት አገልግሎት ስንደል ባለድርሻ አካላት በተቋሙ ላይ በሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅዕኖዎች መሰረት ፍላጎታቸዉን የመለየትና የመተንተን ሥራ በሚከተለዉ ሰንጠረዥ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡-የተቋሙ የተገልጋዮችና የባለድርሻ አካላት ልዩታ**

| ተገልጋዮች/ደንበኞች | ባለድርሻ አካላት |
|---|---|
| ባለሃብት | ክልል ም/ቤት |
| ህብረተሰቡ | ክልሉ መስ/ም/ቤት |
| በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች | ኢንቨስትመንት ቦርድ |
| | የአካ/ደ/አየር/ን/ለውጥ ባለስልጣን |
| | ከተማ አስተዳደር |
| | ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች |
| | ገቢዎች ባለስልጣን |
| | ፋይናንስ ቢሮ |
| | መሬት አስተዳደርና ማህበራት ማደራጃ ቢሮ |
| | ፕላንና ልማት ቢሮ |
| | ግብርና ቢሮ |
| | የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ |
| | የሥራና ክህሎት ቢሮ |
| | መሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት (ቴሌ፣መብራት ኃይል፣ መንገድ፣ ባንኮች) |
| | ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ |
| | ኢንቨስትመንት ኮሚሽን |
| | ጉሙሩክ ኮሚሽን |
| | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር |
| | የኢንዱስትሪ ግብአቶች ልማት ድርጅት(ኢ.ግ.ል.ድ) |
| | የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት |
| | ገንዘብ ሚንስተር |
| | ሚዲያዎች |
| | ባህልና ቱሪዝም ቢሮ |
| | የዲያስፖራ ጉዳዮች ፅ/ቤት |
| | ሰላም ግንባታ ቢሮ |
| | የዞን/የከተማ አስተዳሮች እና ወረዳዎች የን/ኢ/መምሪያዎች /ጽ/ቤቶች |

**ሠንጠረዥ 2፡- ተገልጋዮችልዩታናፍላጎቶቻቸዉ**

| ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት፤ | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የሚፈልገው ባህርያት | የተገልጋዮች / ባለድርሻ አካላት ፍላጎት / አገልግሎት፤ | ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች፤ | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የተፅዕኖ ደረጃ /ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ/፤ |
|---|---|---|---|---|
| **ተገልጋዮች** | | | | |
| ህብረተረሰብ | ▪ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲያከብሩ<br>▪ የልማቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ<br>▪ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና ተጠቃሚ መሆን | ▪ ተኪ ማግኘት<br>▪ የስራ ዕድል እንዲፈጠር<br>▪ ቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠርላቸዉ | ▪ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት አይስፋፋም | ከፍተኛ |
| ባለሀብት | ▪ ልማታዊ ባለሀብት እንዲሆኑ<br>▪ በገቡት ዉል መሰረት የልማት ስራቸዉን እንዲያከናዉኑ<br>▪ አዋጅ፣ደንቦችና መመሪያወች ተግባራዊ እንዲደረጉ፣ | ▪ ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸዉ<br>▪ ታዓማኒነት፣ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ዉጤታማ አገልግሎት እንዲኖር<br>▪ ዋስትና ጥበቃ ይፈልጋሉ<br>▪ የኢንቨስትመንት መረጃ<br>▪ ስልጠናና ድጋፍ<br>▪ የዉይይት መድረክ ይፈልጋሉ | ▪ አመኔታ ማጣት፣<br>▪ ሪ-ኢንቨስት አለማድረግ፣<br>▪ ፈጥነዉ ወደ ስራ አለመግባት፣፤<br>▪ ገፅታ ማበላሸት<br>▪ የፕሮጀክት አፈፃፀም መጓተትና መቋረጥ | ከፍተኛ |
| በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች | ▪ አምራች ባለሀብት እንዲሆኑ<br>▪ በገቡት ዉል መሰረት የልማት ስራቸዉን እንዲያከናዉኑ<br>▪ አዋጅ፣ደንቦችና መመሪያወች ተግባራዊ እንዲደረጉ፣ | • ወቅታዊ የኢንዱስተሪ መረጃ አገልግሎት ፣<br>• ስልጠና፣ ድጋፍና የምክር አገልግሎት፣<br>• መሸጫ እና መስሪያ ቦታ ማግኘት | ▪ አመኔታ ማጣት፣<br>▪ ፈጥነዉ ወደ ስራ አለመግባት፣፤<br>▪ ገፅታ ማበላሸት<br>▪ የፕሮጀክት አፈፃፀም መጓተትና መቋረጥ | ከፍተኛ |

## ሠንጠረዥ 3፡- የባለድርሻ አካላት ልዬታና ፍላጎቶቻቸዉ

| ባለድርሻ አካላት፤ | ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት የሚፈልገው | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት (ምርት/አገልግሎት)፤ | ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች፤ | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የተፅዕኖ ደረጃ /ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ/፤ |
|---|---|---|---|---|
| | | **ባለድረሻ አካላት** | | |
| ***የክልል ም/ቤት*** | ▪ የህግ ማዕቀፎችን ማጽደቅ፣<br>▪ ግምገማ እና ወቅታዊ ግብረ መልስ ማግኘት፣<br>▪ በቂ ሃብት መመደብ ፖሊሲዎችን፣ እስትራቴጅዎችን፣ ህጎችንና ደንቦችን ማስተግበር ፣ | ▪ የመንግስት ህጎች፣አዋጆችና ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ማስተግበር<br>▪ ለህብረተሰቡ ተጠያቂ መሆንን ማረጋገጥ፣<br>▪ ዕቅድና ሪፖርት በወቅቱ ማቅረብ | ▪ የተሰጠውን ተልዕኮ መወጣት ባይችል የአመኔታ መቀነስ<br>▪ ተቋሙን ከሌላ ጋር ማዋሃድ፣ሚናውን የመቀየር ወይም እንዲዘጋ ማድረግ | ከፍተኛ |
| የክልሉ መስ/ም/ቤት | ▪ በጀት በአጋባቡ እንዲመደብ<br>▪ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲፀድቁ | ▪ በሚዘጋጁ የዉይይት መድረኮች የሥራ አመራር እንዲተላለፍ<br>▪ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ<br>▪ ወቅታዊ የኢንዱስትሪና የኢንቨስትመንት መረጃዎች ይፈልጋል<br>▪ የክልሉ የሀብት አማራጭ እንዲለዩ እንዲተዋወቁና ጥቅም ላይ እንዲውሉ<br>▪ ደንበኛ ተኮር አገልግሎት በመስጠት | ▪ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መዳከም | ከፍተኛ |
| ኢንቨስትመንት ቦርድ | ▪ በወቅቱ ውሳኔ እንዲሰጡ | ▪ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲተገበሩ<br>▪ አጀንዳዎች ተቀርፀዉ እንዲቀርቡ<br>▪ ዉሳኔዎች እንዲተገበሩ | ▪ ቅሬታዎች ይበዛሉ<br>▪ ወቅታዊ ምላሽ አለመስጠት | ከፍተኛ |
| መሬት አስተዳደርና ማህበራት ማደራጃ ቢሮ | ▪ የኢንቨስትመንት መሬት መረጃ<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር<br>▪ የጋራ ዉይይት መድረክ (ፎረም)<br>▪ ለኢንቨስትመንት ተለይተዉ የተዋወቁ መሬት አሰራሩን ጠብቆ እንዲተላለፍ | ▪ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች እንዲሰሩ<br>▪ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራ | ▪ ቅንጅታዊ የስራ ግንኙነት ይሻክራል<br>▪ ኢንቨስትመንት አይስፋፋም<br>▪ የተቋሙ ገጽታ ይበላሻል | ከፍተኛ |

| ባለድርሻ አካላት፤ | ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት የሚፈልገው | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት (ምርት/አገልግሎት)፤ | ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች፤ | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የተፅዕኖ ደረጃ /ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ/፤ |
|---|---|---|---|---|
| የአካ/ደ/አየር/ን/ለውጥ ባለስልጣን | ▪ የአካባቢ ተፅዕኖ ገምግሞ ማቅረብ፣<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር<br>▪ የጋራ ዉይይት መድረክ (ፎረም) | ▪ የጥናት ሰነዱ እንዲተገበር | ▪ ቅንጅታዊ የስራ ግንኙነት ይሻክራል<br>▪ ኢንቨስትመንት አይስፋፋም<br>▪ የተቋሙ ገጽታ ይበላሻል | ከፍተኛ |
| የከተማ አስተዳደርና ማዘጋጃ ቤቶች | ▪ የኢንቨስትመንት መሬት መረጃ<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር<br>▪ የጋራ ዉይይት መድረክ (ፎረም)<br>▪ ለኢንቨስትመንት ተለይተዉ የተዋወቁ መሬት አሰራሩን ጠብቆ እንዲተላለፍ | ▪ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች እንዲሰሩ<br>▪ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራ | ▪ ቅንጅታዊ የስራ ግንኙነት ይሻክራል<br>▪ ኢንቨስትመንት አይስፋፋም<br>▪ የተቋሙ ገጽታ ይበላሻል | ከፍተኛ |
| ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ | ▪ የመሬት መረጃ<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር<br>▪ የጋራ ዉይይት መድረክ (ፎረም)<br>▪ ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተለይተዉ የተዋወቁ መሬት አሰራሩን ጠብቆ እንዲተላለፍ | ▪ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች እንዲሰሩ<br>▪ የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራ | ▪ ቅንጅታዊ የስራ ግንኙነት ይሻክራል<br>▪ ኢንቨስትመንት አይስፋፋም<br>▪ የተቋሙ ገጽታ ይበላሻል | ከፍተኛ |
| የክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን | ▪ መረጃዎች<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር ይፈልጋል | ▪ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ግብር እንዲሰበሰብ | ▪ የገቢ መቀነስ | ከፍተኛ |
| ፋይናንስ ቢሮ | ▪ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡<br>▪ የፀደቀውን በጀት በወቅቱ ማስተላለፍ፡፡ | ▪ የአሠራር ስርዓትን መሠረት በማድረግ የተመደበ በጀትን ለታቀዱ ተግባራት በወቅቱ ስራ ላይ ማዋል | ▪ ገንዘብና ንብረት ያላግባብ ይባክናል<br>▪ ወቅቱን ያልጠበቀ በጀት አጠቃቀም ይከሰታል፡፡<br>▪ ዕቅድ፣ ሪፖርትና መረጃዎቹን በወቅቱ ማቅረብ አይቻልም | ▪ ከፍተኛ |
| ***ፕላንና ልማት ኮሚሽን*** | • የዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገ፣ማ ሥርዓት ይዘረጋል<br>• ከፌድራል ፕላን ልማት ኮሚሽ የሚመጡ ሀገራዊ የትኩረት አቅጣጫዎችን ወደ ክልላዊ ነባራዊ ሁኔታ ይቀይራል የስተባብራል | • የተናበበና የደራጀ ዕቅድና ሪፖርት በወቅቱ መላክ<br>• ወቅታዊና ታዓማኒነት ያላቸውን መረጃዎች አደራጅቶ መላክ | • የተቋሙ በጀት ሊከለከል ይችላል<br>• በተናበበውና በተፈራረመው ልክ ተጠያቂነት ይሰፍናል | ከፍተኛ |
| | • የአቅምግንባታና የመልካም አስተዳደርሥራዎችን ቀጣይነትና ተከታታይነት እንዲኖረው ማድረግ | ▪ መዋቅሮችን አደረጃጀት በመፈተሽ አጥንቶ ማቅረብ፤ | • የሠራተኞች የሥራ ተነሳሽነት መቀነስ፣ | ከፍተኛ |

| ባለድርሻ አካላት፤ | ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት የሚፈልገው | የተገል.ጋዮች/ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት (ምርት/አገልግሎት)፤ | ተገል.ጋዮች/ ባለድርሻ አካላት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች፤ | የተገል.ጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የተፅዕኖ ደረጃ /ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ/፤ |
|---|---|---|---|---|
| ***ሲቪል ሰርቪስኮሚሽ*** | • የተቋሙን የሰው ሀይል መዋቅር በጥናቱ መሰረት መፍቀድ፣ | ▪ የወጡ የሕግ ማዕቀፎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡<br>▪ ትክክለኛና ወቅታዊ የሰው ሃይል መረጃ ማጠናከር፣ | • ልማት ይጓተታል፣ | |
| ***ግብርና ቢሮ*** | • በግብርናው መስክ ለተሰማሩ የዘርፉ ባለሀብቶች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣<br>• ወቅታዊ የቅድመ ምርትና ድህረ ምርት የመረጃ ልውውጥ ፣<br>• ቅንጅተዊ አሰራርና መልካም ግንኙነት እንዲኖር ፣ | ▪ ለትስስር የሚረዱ መረጃዎችን ማዘጋጀትና ማቅረብ፣<br>▪ በአግሮ ኢንዱስትሪ መስክ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ምቹ የስራ ሁኔታ እንዲፈጠር<br>▪ አርሶ አደሩ ላመረተው ገበያ ተኮር የሆኑ የገብርና ምርቶች የገበያ ትስስር እና የዋጋ መረጃ አገልግሎት እንዲያገኙ፣ | • የወጭና ገቢ ንግድ ሚዛን ይዛባል፣<br>• ለሸማቹ ህብረተሰብ በቂ የግብርና ምርት አለመኖር፣<br>• አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች በቂ ምርት አለማቅረብና ምቹ የስራ ቦታ አለመኖር፣ | ከፍተኛ |
| ***የሥራና ክህሎት ቢሮ*** | • በጥ/አ/ኢ/የተደራጁ ማህበራት ወደ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪ እንዲሸገሩ መደገፍና ማጠናከር፣<br>• ብቃት ይሰጣል<br>• የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል | ▪ ወደ አነስተኛ እና መካካለኛ ኢንዱስትሪ የተሻገሩትን ማህበራት መደገፍና መከታተል፣<br>▪ ብቃት ለተሠጣቸው አካላት የንግድ ፍቃድ መስጠት | የኢንዱስትሪ ልማትን ያጓትታል፣ | ***ከፍተኛ*** |
| መሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት (ቴሌ፣መብራት ኃይል፣ መንገድ፣ ባንኮች) | • ለዘርፎቹ ልማት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት፣ በተፈለጉበት ጊዜ አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ፡<br>• የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፤ | ▪ በመሠረተ ልማት ዙሪያ ብልሽት ሲያጋጥም መረጃ በወቅቱ ማድረስ<br>▪ የቀረቡ መሠረተ ልማቶችን መንከባከብና ተቀናጅቶች መሥራት<br>▪ የመሠረተ ልማት እቅድ ፣ ፍላጎትና ለዝርጋታው የሚሆኑ መረጃዎችን መስጠት፡ | ▪ ያለመሠረተ ልማት የዘርፉን ልማት ማከናወን አይቻልም፡፡<br>▪ የባለሃብቱ እንቅስቃሴ ይገታል፡፡<br>▪ የመረጃ ግንኙነት ይጓተታል፡፡<br>▪ | ▪ ከፍተኛ |
| የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን | ▪ ቅንጅታዊ አሰራር ይፈልጋል<br>▪ የስራ እቅድ ይፈልጋል<br>▪ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ወቅታዊ እንዲሆኑ<br>▪ የአቅም ግንባታ ስራዎችና ማቴሪያል ድጋፍ<br>▪ የጋራ ምክክር መድረክ | ▪ ወቅታዊ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች<br>▪ የጋራ ምክክር መድረክ | ▪ በተዋረድ ያለ ቅንጀታዊ አሰራር ይዳከማል፣<br>▪ የመረጃ ፍልሰት | ከፍተኛ |

| ባለድርሻ አካላት፤ | ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት የሚፈልገው | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት (ምርት/አገልግሎት)፤ | ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች፤ | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የተፅዕኖ ደረጃ /ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ/፤ |
|---|---|---|---|---|
| ኢንዱስትሪ ሚኒስተር | ▪ የግብርና ምርትን በግብአትነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ልዩ ትኩረት ሠጥቶ ማስፋፋት/ አግሮፕሮሰሲንግ/፡፡<br>▪ የስልጠና የድጋፍ አገልግሎት<br>▪ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎችን ማስተግበር፣<br>▪ ቅንጅታዊ አሰራር ፣ | ▪ ወቅታዊ ዕቅዶችና መረጃዎች ልዉዉጥ ፤<br>▪ የአሠራር ሕጎች እንዲወጡና ተግባራዊ እንዲደረጉ መተባበር | ▪ ልማት በተፈለገው መጠን ፣ ጥራትና ፍጥነት ማሳደግ አይቻልም፡፡<br>▪ ለኢንዱስትሪ የተከለሉ ቦታዎችን በብቃትና በፍጥነት የመጠቀም አቅምን ያዳክማል፣ | ከፍተኛ |
| *የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን* | • ወቅታዊ መረጃ እንዲሰጥ፣<br>• ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎችና ማሽነሪዎችን መፍቀድ | ▪ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር የመረጃ ልዉዉጥ፣ | ▪ ልማት በተፈለገው መጠን ፣ ጥራትና ፍጥነት ማሳደግ አይቻልም፡፡ | ከፍተኛ |
| *የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይ ልማት* | • ኢንተርፕሩነር ለመሆን የሚተጉ<br>• ለላቀ ተወዳዳሪነት የሚተጉ<br>• ተኪ እና ወጪ ምርቶችን በጥራት እንዲያመርቱ<br>• ለከፍተኛ ኢንዱስትሪ መሰረት እንዲሆኑ<br>• ልማታዊ አስተሳሰብ እንዲኖራቸዉ | • ግልጽ፤ፍትሀዊ፤አሳታፊና ተጠያቂ ያለዉ አሰራር<br>• ክፍተትን መሰረት ያደረገ መንግስታዊ ድጋፎችን<br>• ቀልጣፋና ዉጤታማ አገልግሎት | • አመኔታ ማጣት<br>• ለኢኮኖሚዉ ማበርከት የሚገባቸዉ አስተዋጽኦ ዝቅተኛ በመሆኑ የቢሮዉ ህልዉና አጠያያቂ መሆን | መካከለኛ |
| *ቤ/ጉ/ክ/መ ህዝብ ግንኙነት ፕሮቶኮል እና ዲያስፖራዎች ጉዳይ ቢሮ* | • ዲያስፖራዎች በልማቱ እንዲሳተፉ መደገፍ እና መሳብ<br>• ቅንጅታዊ ስራዎች<br>• የቴክኖሎጅ ሽግግር ማድረግ፤ | • የተመቻቸ የኢንዱስትሪ ክላስተር<br>• የገበያ ትስስር፤<br>• ቀጣይነት የሆነ ክትትልና ድጋፍ | • ልማትን ያጓትታል፤<br>• ስራ አጥነትን ይጨምራ፤<br>• የዉጭ ምንዛሬ ላይ ተፅዕኖ ያደርሳል፣ | መካከለኛ |
| *የዞን/የከተማ አስተዳሮች እና ወረዳዎች የን/ኢ/መምሪያዎች/ጽ/ ቤቶች* | • ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ<br>• ተናባቢ የሆነ እቅድ እና አፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርቡ<br>• ዘርፉን የተመለከቱ መረጃዎች በጥራትና በወቅቱ በማሰባሰብና በማደራጀት እንዲልኩ<br>• የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በየዘርፉ እንዲያደራጁና እንዲደግፉ<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተዉ ኢንዱስትሪዎች ዉጤታማ የሆነ ድጋፎችን እንዲያገኙ | • የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፤ የህግና የድጋፍ ማእቀፎች፤ልዩ ልዩ መመሪያዎችና ማኑዋሎች<br>• የአቅም ግባታ ድጋፍ<br>• የገበያ ትስስር<br>• የማምረቻና የመሸጫ ክላስተሮች ዲዛይን<br>• የተቀመሩ ምርጥ ተሞክሮዎች | • የዕቅድ አለመሳካት<br>• እዉቅና፤ተብብርና ድጋፍ መንፈግ<br>• የቢሮዉን ተልእኮ ባለማሳካት ህልዉናዉን አጠያያቂ ማድረግ | ከፍተኛ |

## 6.3. የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ ትንተና

??? ??? ????? ? ???? ? ? ? ????? ???? ????????? ??? ??? ????? ??? ????? ???? ?? ??? ?? ?? ??? ???? ????? ?? ??? ???? ????? ?? ? ???? ?? ? ?? ? ??? ???? ????? ?? ??? ????? (????) ?? ???? (???) ???? ???? ?? ????? ?? ?? ?? ???? ?? ??? ? ? ? ? ??????? ????? ????? ?? ? ??? ??? ??? ? ?? ?? ?? ???????

??? ? ??? ???? ?????? ??????? ? ?? ?? ????? ???? ??????? ??????? ???????? ??????? ?? ??????????????????????? ? ???? ?????? ????? ???? ????? ??? ? ??? ??????? ? ???? ?? ??? ??? ? ????? ????????? ?????? ???? ???? ?? ??? ???? ?? ???? ????? ?????

## ሠንጠረዥ 4፡- የውስጣዊሁኔታትንተና

| ? .? | ?? ?? ?? ? ?? ?? | ? ??? ?? | ??? ?? |
|---|---|---|---|
| 1 | ?????? | • ?? ? ???? ???? ???? ?????? ??? ? ???? | • ????? ?? ???? ? ? ??? ?? ? ????? ? ??? ?? ? ?? ?? ? ? ?? ? ???? ??? ?? ??? ???? |
| 2 | ????? ??? | • ?? ???? ??? ??? ?? ? ????? ? ???? ? ???????? ? ??? ???? ???? ???? ? ?? ?? | • ??? ?? ???? ??? ?? ??? ???? ?????? ??? ????????? ?? ?? ??? ? ???-? ?? ???? ??? ? ??? <br>• ?? ?? ?????????????????? ????? ??? ? ?? |
| 2 | ??????? ???? | • ???? ????? ???? ???? ?? ??? ??? ?? ???? ??????? ???? ?? ??? ????? <br>• ?????? ?? ??? ????? ???? ?? ???? ?? ? ??? ?? ???? ?? ? ???? ???? | • ??? ?? ?? ?????? ?????? ??? ????? ? ?? ??? ??? <br>• ?? ?? ??????? ? ???? /?? ????/ ?? ??? ??????? ???? ??? ??? ?? ???? ??? ??? ? ??? ???? ?? ??? ??? ??? ??? ??? |
| 3 | ????? ??? | • ??? ? ?? ??? ??? ???? ? ?? ? <br>• ??? ??? ????? ?????? ? ??? | • ????? ???? ???? ??? ???? ? ??? ??? ?? |
| 4 | ??? ?? ??? | • ???? ???? ? ??? ?? ?? ?? ?? ? ???? | • ???????? ??? ?? ??? ??? ?? <br>• ??? ??? ????? ?? ?????? ?????? ?? ??? ? ???? ? ?? |
| 5 | ????? | • ?????? ??? ????? ?? ?? ??? ????? ? ?? ???????? ??? ?? ????? ????? ????? ? ??? | • ?????? ??????? ?? ???? ?? ?? ????? ??? ??? ???? <br>• ??? ???? ????? ? ?? ?????? ???? |

| ? .? | ?? ?? ?? ? ?? ?? | ? ??? ?? | ??? ?? |
|---|---|---|---|
| | | | ? ???? ????? ??? ? ??? |
| 6 | ? ? ? ? ? ? | • ?? ? ? ??? ?? ? ??? ? ??? ? ?? ? ???????? ? ??? ? ????? | • ?? ? ? ? ?? ???? ? ?? ??? ?? ? ??? ? ??? ??? <br>• ?? ? ? ? ? ??? ? ??? ? ??? ?? ???? ?? ???? ??? ? ??????? ? ? ? ? ???? ? ??? ??? |
| 7 | ? ?? ? ??? | • ? ?? ??? ??? ??? ?? ? ??? <br>• ?? ? ?????? ?? ? ? ?? ?? ? ?????? ? ? ? ? | • ?? ? ??? ? ? ????? ? ??? ??? ? ???? ? <br>• ?? ?? ?? ? ? ????? ??????? ?? ? ?? ? ? ? ??? ??? <br>• ? ? ??? ?? ?? ?? ?? ???? ??? ?? ? ?? ? ??? ??? ?? <br>• ?? ???? ? ??? ??? ??? ? ?? |
| 8 | ? ? ??? | • ? ???? ???? ? ???? ?? ? ? ??? ? ? ?? | • ?? ???? ??? ?? ??? ?? <br>• ??? ? ?? ? ?? ???? ? ???? ? ??? |

## ሠንጠረዥ 5፡- ውጫዊ ሁኔታ ትንተና

| ?.? | ?? ? ??<br>? ???? | ? ??? ?????? ? | ???? |
|---|---|---|---|
| 1 | ? ????? ???<br>? ?? | • ???? ? ?? ?? ? ? ????? ? ?? ? ? ???? ? ???<br>• ????? ???? ? ? ??? ????????? ? ????<br>? ?????? ?<br>• ????????? ? ??? ???? ??? ??? ?? ?? ??????<br>?? ? ? ? ???? ? ? ??? ? ????<br>• ?????? ????? ???/???/? ? ? ???? ???<br>? ??/? ??? ????? ? ??/?<br>• ? ??? ?????? ?? ??? ?????? ?? ?? ???? ?? ?<br>??? ??? ???? ? ? ???? ? ????<br>• ?? ???? ?????? ???? ?? ??? ???? ??? ??<br>???? ? ? ??? | • ??? ???? ?? ?? ???? ??? ??? ??? ????<br>??? ?????<br>• ????? ??? ?? ??? ??? ?? ???? ??? ????<br>???? ?????? ??? ???? ??? ????<br>• ?? ? ? ???? ?????? ?? ??? ?? ??? ????<br>????? ??? ?? |
| 2 | ? ??? ?? | • ? ? ?? ?? ??? ???? ? ??<br>• ??? ?? ? ? ????? ??? ?? ?? ? ? ??<br>• ? ??? ?????? ???? ?? ?? ???? ????<br>? ?? ? ?? ? ? ? ?<br>• ??? ???? ?? ????? ? ??<br>• ?? ??? ??? ?????? ?????? ? ??<br>• ?????? ?????? ??? ?? ??? ?? ?? ? ? ??? | • ???? ?? ???? ? ??<br>1. ?? ?? ???????? ??? ? ? ??? ???? ?? ?? ???<br>??? ??? ??? |
| 3 | ? ???? | • ?? ?? ?? ?? ? ????? ?? ? ???? ???? ? ????? ?<br>????? ? ?? ???? ? ?? | 2. ?? ???? ? ?? ???? ???? ? ??? ?? ?? ??<br>???? ??? ?? |
| 4 | ?????? | • ?? ?? ?? ?? ? ????? ?? ? ???? ?? ? ? ????<br>?? ?? ? ? ????<br>• ??? ???? ?? ????? ?? ? ? ? ?? | 3. ?? ????? ?? ???? ???? ? ? ? ??? ??? ????<br>4. ????? ???? ?????? ?? ??? ?????? ?? ????<br>???? ???? |
| 5 | ? ???? | • ?????? ?? ?? ?? ?? ? ????? ?? ? ???? ???<br>???? ??? ? ? ? ?? | 5. ???? ??? ? ? ? ? ?? ???? ?? ?? ???<br>6. ??/?? ??? ??? ????? ? ?? |

## 6.4. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ትንተና

በውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ የተለዩ ጥንካሬዎችን፣ ድክመቶችን፣ መልካም አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን (SWOT) መነሻ በማድረግ፣ የተቋሙን ውስጣዊ ጥንካሬና የውጫዊ መልካም አጋጣሚዎችን በመገምገም፣ አስቻይ ሁኔታዎችን (Enablers) እንዲሁም ከውስጣዊ ድክመቶችና ከውጫዊ ስጋቶች የሚመነጩ ፈታኝ ሁኔታዎች (Pains) በመለየት እንደሚከተለው ተጠቃሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 6፡- የአስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ትንተና**

| | ???? ????? /????+? ??? ???? / | ??? ????? /??? ?+ ???/ |
|---|---|---|
| | • ????? ? ???? ?????? ?? ?? ??? ? ???? ? ?????? ???? ???? ??? ? ?? ? ??? ??<br>• ??? ?????? ??? ????? ?? ?? ??? ????? ? ?? ? ?????<br>• ? ???? ?? ?? ?? ?? ? ????? ?? ? ???? ???? ???? ? ???<br>• ? ??? ??? ???? ? ????<br>• ?? ?? ?? ?? ? ????? ?? ? ? ??? ??? ? ?? ?????? ? ???<br>• ??? ??? ???? ?? ? ????<br>• ? ?? ??? ??? ??? ?? ? ??<br>• ??? ?? ??? ?? ?? ????? ?????? ? ??<br>• ????? ?? ??? ?? ?? ? ? ??<br>• ?? ??? ? ? ?? (??? ) ? ???<br>• ????? ???? ? ???? ? ?? ??? | • ?? ? ?? ?? ???? ? ???<br>• ?? ??? ?????? ???<br>• ? ????? ??? ?? ?? ??? ??? ?????? ?? ???? ? ??? ??? ??<br>• ?????? ?? ??????? ? ??? ????? ????? ??? ?????? ? ?? ???? ??? ???? ?? ?? ?? ?? ? ??? ??? ???? ????? ??? ??? ????? ??? ?? ???? ? ?????<br>• ?? ? ?? ??? ? ??? ?????<br>• ?? ?? ???? ?? ???? ??? ? ???? ? ??<br>• ??????? ??? ???? ???? ??? ???? ???? ???? ?? ??? ??? ? ??<br>• ?? ?? ???? ??? ?? ????? ??? ???? ????? ??? ???<br>• ?? ? ??? ??? ? ???<br>• ???? ???? ??? ??? ???? ???? ? ??? ???? ?? ????? ?? ??? ???<br>• ??? ?? ??? ????? ??? ??? ?? |

## 6.5. ትኩረት የሚሹ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

- ? ? ? ??? ??? ?? ? ?? ? ? ? ?? ?? ? ?? ? ? ? ?? ?? ??? ??? ? ???
- ??? ??? ?????? ? ?? ? ? ? ???? ?? ? ??? ? ?? ?? ??? ? ? ??
- ?? ? ? ? ???? ? ???? ? ?? ??? ??? ?? ?? ? ??? ? ? ? ? ?? ? ???
- ?? ?? ?? ?? ? ???? ? ?? ?? ? ?? ? ? ??? ?? ? ?? ? ? ? ? ???? ? ? ? ? ??
- ???? ? ? ?? ???? ? ?? ??? ?? ? ? ? ?? ? ? ? ? ?? ? ??? ? ? ???? ? ????
- ?? ?? ?? ?? ? ?? ???? ? ?? ?? ?? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ?? ? ?? ? ? ? ??? ? ??? ? ? ? ???? ? ????
- ???? ?? ???? ? ?? ????? ? ?? ? ? ? ? ??? ?? ?? ? ??? ? ? ??
- ?? ?? ?? ? ? ? ? ?? ? ??? ??? ? ?? ? ?

# 7. የቢሮዉ ተልዕኮ፣ራዕይ እና እሴቶች

## 7.1. ተልዕኮ /Mission/

?? ? ? ?? ?? ?? ?? ? ???? ? ?? ?? ? ?? ? ? ? ? ?? ??? ? ? ???? ?? ?? ???? ?? ? ??? ?? ???? ? ? ? ?? ? ??? ?? ? ??? ?? ??? ???? ???? ?? ?? ??? ?? ??? ???? ?? ????? ???? ?? ??? ??? ? ? ? ????? ?? ? ? ? ?? ?? ? ? ???? ? ?? ? ? ???? ??

## 7.2. ራዕይ /vision/፣

?2022 ??? ? ? ? ?? ?? ? ???? ?? ? ? ?? ?? ?? ? ???? ? ?? ? ???? ? ?? ?? ??

## 7.3. እሴት /values/

- ? ??? ? ?? ? ????
- ??? ? ? ? ? ?
- ?? ? ? ? ? ? ? ? ??
- ?? ??? ?? ? ?? ? ??? ? ?? ? ??? ? ? ? ? ?
- ? ?? ??? ??? ? ???

## 8. ለተቋሙ በአዋጅ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት

1. ?? ????? ?? ? ???? ? ?? ??? ??? ?? ? ?? ? ?? ? ? ??? ?? ? ??????
2. ?? ??????? ??? ? ? ????? ? ??? ?? ?? ? ?????? ? ? ? ?? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ??? ??? ? ? ? ??? ??? ???? ???? ? ??? ?? ??? ?? ? ? ?? ?? ????
3. ??? ?? ???? ? ? ?? ? ??? ?? ???? ? ? ???? ?? ?? ?? ? ? ?? ?? ???? ? ??? ?? ? ??? ? ???? ??????
4. ??? ???? ? ?? ?? ? ? ???? ? ?? ??? ??? ? ? ?? ?? ??? ? ??? ?? ? ?????? ?? ??? ????
5. ?? ????? ?? ???? ? ?? ? ???? ? ? ?? ? ???? ??? ? ?? ???? ? ?? ????? ???? ? ??? ?? ????? ? ????? ? ????? ?? ??? ? ?? ?? ???? ? ?? ? ? ? ???? ? ????? ? ?? ? ??? ???? ?? ?? ? ? ??????? ?? ? ??????
6. ??? ? ??? ? ? ???? ?? ???? ? ?? ??? ??? ?? ??? ??? ? ? ? ? ??? ? ?? ?? ???? ???? ? ????? ? ?? ?? ?? ? ? ??? ??????
7. ?? ???? ? ?? ??? ?? ?? ? ? ??? ?? ???? ? ?? ????? ? ?? ?? ? ???? ? ???? ? ? ?? ?????????? ??? ? ? ? ? ? ?????? ???? ?? ?? ? ? ?? ? ??? ??? ? ?? ??????
8. ?? ???? ? ?? ? ? ? ?? ?? ?? ? ?ሆ???? ?? ????? ?? ??? ? ? ??? ? ???? ???? ? ? ?? ????? ?? ??? ???? ? ???? ? ????? ???? ? ? ? ? ?????
9. ??? ? ? ?? ?? ??? ? ???? ?? ??? ?? ???? ? ?? ??? ? ??? ?? ?????? ? ?? ????? ? ??? ?? ??????? ??? ? ?? ?? ?? ?? ???? ? ?? ?? ???? ? ????? ???
10. ? ???? ? ?? ?? ???? ?? ?? ???????? ????? ?? ? ?? ?? ? ? ? ? ???? ?? ??? ? ? ??????? ???? ? ???? ? ? ?????
11. ??? ? ? ?? ?? ???? ? ?? ???? ? ?? ????? ? ??? ??? ? ?? ? ? ?? ??? ?? ?? ????? ? ?????

12.??? ? ? ?? ???? ?? ? ? ? ?? ????? ? ?? ?? ? ? ??? ?? ? ??? ? ??? ? ????? ? ? ????? ? ????? ? ?? ?????? ?? ???? ????? ? ???? ??? ?? ?? ? ? ???? ??? ??? ?? ? ? ?

13.??? ? ????? ?? ? ?? ???? ???????? ? ???? ? ? ??? ??? ?? ??? ? ? ????? ?? ? ?? ? ??? ?????? ??? ? ???? ? ?? ??? ?? ? ? ??? ??? ?? ????? ??????? ??? ? ? ? ? ?

14.?? ? ??? ? ? ???? ? ? ?? ? ?? ?? ?? ? ? ???? ? ???? ? ?? ?? ?? ?? ? ? ? ? ????? ??? ? ? ?? ?? ????? ???? ? ?? ? ? ? ?? ? ??? ??????? ?? ? ???? ? ??? ? ? ? ?

15.??? ? ?? ?? ?? ? ? ??? ??? ? ? ??? ?? ? ?? ? ?? ? ? ?? ? ? ?? ?? ???? ??? ??? ??? ? ? ? ? ?

16.??????? ??? ??? ?? ? ????? ? ? ? ??? ? ??? ? ? ?

17.?????? ?? ?? ???? ?? ? ? ? ?? ?? ?? ? ???? ? ??? ? ??? ?? ? ??? ??? ? ? ? ? ???? ?

18.??? ?? ???? ? ? ?? ? ??? ? ??? ? ? ????? ?? ? ?? ? ???? ? ??? ?

19.??? ? ? ?? ?? ?? ?? ????? ? ? ? ????? ? ???? ?? ?

# ደረጃ ሁለት

## 2. ስትራቴጅያዊ የትኩረትመስኮች፣ውጤቶች እና እይታዎች

በዚህ ደረጃ ከውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና እና ከተገልጋዮችና ከባለድርሻ አካላት ፍላጎቶች ትኩረት የሚሹ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮችን በመለየት የተቋሙን ዋና ዋና ተግባራት፣ የስኬት አምድ /Pillars of excellence/፣ ራዕይን ወደ ውጤት የሚያሸጋግሩ ትስስርን ለመፍጠር የሚያችሉ፣ ከተቋም ተቋማት ጋር የተዛመዱ ወደ መጨረሻ ውጤት /Final outcome/ ለመድረስ ምን መፈጸም እንዳለበት የሚያመላክቱ **ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችን** የመለየትና እነዚህ ሲሳኩ የሚገኙ **ስትራቴጂያዊ ዉጤቶችን** የማስቀመጥ እንዲሁም የተቋም አፈጻጸም ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር ለማየት የሚያስችሉ **ዕይታዎችን** የመለየት ስራ ተሰርቷል ፡፡

**የዘርፉ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና የተመረጡ ዕይታዎች**

### 2.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂያዊ ውጤቶች |
|---|---|---|
| 2 | ያደገ የኢንዱስትሪ ልማት | ያደገ የኢንዱስትሪ ተጠቃሚነት |
| 3 | የላቀ ኢንቨስትመንትን ልማት፣ | ያደገ ኢንቨስትመንት ፍሰት |
| 4 | ስትራቴጂያዊ አጋርነት | የጎለበተ ቅንጅታዊ የአሰራር ግንኙነት |
| 5 | የላቀ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም መገንባት | ያደገ የማስፈጸም እና የመፈጸም አቅም |

## 2.2. የስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች መግለጫ

ሠንጠረዥ 6 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ ዉጤትና መግለጫ

| የትኩረት መስክ | ክብደት በ% | ወሰን | የትኩረትመስኩ ውጤት |
|---|---|---|---|
| ያደገ የኢንዱስትሪ ልማት | 40 | ▪ የኢንዱስትሪ ልማት ለማሳደግ በኮንስትራክሽን፣በንግድና አገልግሎት ዘርፍ የተሠማሩ የክልሉ ውስጥ ባለሀብቶችን በመመልመል ወደ ማኑፈክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በማስገባት፤ጉልበትን በሰፊው ለሚጠቀሙና ሰፊ ገበያ ላላቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ በመስጠት፤ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር እና በማስፋፋት<br>▪ አዲስ የሚቋቋሙ እና ነባር ኢንዱስትሪዎች ክፍተትን መሰረት ያደረገ መንግስታዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ማመቻቸት እና እንዲሸጋገሩ በማድረግ፤ ዘርፉን በማጠናከር በሚጠበቀው ልክ ቋሚ የስራ እድል እንዲፈጠር ለማድረግ የሚሰራ ትኩረት መስክ ነዉ | ያደገ የኢንዱስትሪ ተጠቃሚነት |
| የላቀ ኢንቨስትመንትን ልማት | 40 | ▪ የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጭ ጥናት በማድረግ ተጠናከረ የፕሮሞሽን ሥራ በመሥራት ባለሃብቶች በኢንቨስትመንት መስክ እንዲሰማሩ ማድረግ፡፡<br>▪ ልማታዊ ባለሀብቶች ለሚያካሂዱት ኢንቨስትመንት ስራ አፈፃፀም የሚረዳ ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ እንዲፈጠር ማድረግ፤<br>▪ ልማታዊ ባለሀብቶች የሚያስፈልጓቸውን የኢንቨስትመንት ካፒታል እንዲያገኙ የሚያስችል የብድር አቅርቦት ማመቻቸት፣<br>▪ የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ መስጠት፣<br>▪ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት መስኩ በብዛት እንዲሰማሩ በማድረግ ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማፋጠን፣ | ያደገ ኢንቨስትመንት ፍሰት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ▪ ወደማምረት/አገልግሎት መስጠት የሚሸጋገሩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችንና በዳግም ኢንቨስትመንት የሚሰማሩ ባለሀብቶችን ቁጥር ማሳደግ፣ | |
| ስትራቴጂያዊ አጋርነት | 10 | ▪ የተቋሙ ስራዎችን ለማከናወን የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን በማጠናከር አፈፃፀምን ከፍ ማድረግ<br>▪ የልማታዊ ባለሃብቶች እርካታን ለማሻሻልና ተግዳሮቶችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ የዉይይት መድረክ መፍጠር<br>▪ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ስርዓት ለመዘርጋት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት<br>▪ የዳበረ አጋርነት በመፍጠር ወጥነት ያለዉ ችግር አፈታት ስርዓት መዘርጋት | የጎለበተ ቅንጅታዊ አሰራር ግንኙነት |
| የላቀ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም | 10 | ▪ የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም ለመገንባት የሰው ኃይሉን የመፈፀምና የማስፈፀም እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በየደረጃው ለማጎልበት፤ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ግብዓትና አሰራርን ለማሻሻል፤የጥናት እና የምርምር ሥራዎችን አቅም ለማሳደግ፤ምርጥ ተሞክሮዎችን የመተግበር አቅም ለማሳደግ፤የለውጥና ሪፎርም ስራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ፤ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር፤<br>▪ በሥራ ላይ ያሉ የህግ ማዕቀፎችናየማስፈፀሚያ ማንዋሎች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር፣ውድድርን የሚገድቡ አሠራሮችን በጥናት መለየት እና እርምጃ ለመዉሰድ፤የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም ለማሳደግ፤ዘርፈ ብዙ ስራዎችን ለማጠናከር፣የመረጃ ሥራ አመራር ሥርዓትን ማጠናከርና ለማዘመን፤የግሉን ዘርፍ አቅም ለማሳደግ የተጣለ የትኩረት መስክ ነው፡፡ | ያደገ የማስፈጸም እና የመፈጸም አቅም |

## 2.3. የትኩረት መስኮች እይታዎች

ስትራቴጂያዊ ግቦችን ለመለየትና ለመወሰን የትኩረት መስክ እይታዎችን በጥልቀት መቃኘት ተገቢ ነው ። እይታዎች የተቋማትን አፈጻጸም ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር ለማየት የሚያስችሉ ሚዛናዊ መነጽሮች ናቸው። በመሆኑም አንድ መስሪያ ቤት ለሚያስቀምጣቸው ግቦች በዚህ ላይ ተመስርቶ አካሄዱን አይቶ ከሚያመርተው ምርትና ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር አሰራሩንና አደረጃጀቱን ለመወሰን በሚሰጠው አፅንኦት ልክ የስራዎቹን ግቦች ከተገልጋይ ዕይታ፣ ከበጀት አቅርቦት እይታ፣ ከውስጥ አሠራር እይታ እና ከመማማርና ዕድገት እይታ መፈተሽና መቃኘት ያስፈልገዋል። በመሆኑም የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለህዝብ አገልግሎት ለመጠስት የተቋቋመ በመሆኑ ከሌሎች የግል ድርጅቶችና መንግስታዊ ካልሆኑ ግበረ-ሰናይ ድርጅቶች በተለየ መልኩ እይታዎቹን ማስቀመጥ ይጠበቅበታል። በዚህ መሰረት የተገልጋይ ዕይታ አስቀድሞ፣ የበጀት/አቅርቦት/ እይታን በማስከተል እንዲሁም የውስጥ አሠራር እይታና የመማማርና እድገት በማከታተል በሚከተለው አኳኃን ለመቃኘት ተሞክሯል።

**ሰንጠረዥ7፡ በክልሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ዘርፍ የእይታዎች መግለጫ**

| ተ.ቁ | ዕይታ | የእይታ መግለጫ | የእይታው ትኩረት |
|---|---|---|---|
| 1. | ተገልጋይ/ እርካታ | መንግስት የነደፋቸውን ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣እንዲሁም በየጊዜዉ የሚወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመተግበር ፍትሃዊ፣ሕጋዊ፣ፈጣንና ተደራሽነት ያለው አሰራር በመዘርጋት አገልግሎት በመስጠት ተገልጋዩን ህብረተሰብና የመንግስትን ፍላጎቶች ማርካትን ያመለክታል። | የተገልጋይ እርካታ |
| 2. | በጀት/ፋይ ናንስ/ | የተቋሙን ተልዕኮ ለመወጣት የሚገኘውን ሃብት ቀልጣፋ፣ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ መልኩ በስራ ላይ ማዋል። | ውጤታማ የፋይናስ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3. | የውስጥ አሠራር | የሌብነት አመለካከትንና አስተሳሰብን የሚፀየፍና አክርሮ የሚታገል ዜጋ በመፍጠር፣የውስጥ አሰራር ቀልጣፋ፣ መልካም አስተዳደር ዲሞክራሲያዊ አካሔድ በማስፈን ለቢሮዉ በአዋጅ የተሰጡ ተግባራትን በመፈጸምና በማስፈፀም የዉስጥ ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ለሁሉም ተገልጋይ አገልግሎት መስጠትን ያመለክታል፡፡ | ውጤታማ እና ቀልጣፋ አሰራር |
| 4 | መማማር ና እድገት | ፈጣንና ተለዋዋጭ ነባራዊ ሁኔታንና ቴክኖሎጂን ያገናዘበ ወቅታዊ የተገልጋዩን የአገልገሎት ጥያቄ በሚመልስ መልኩ የተቋሙን የሰው ሀይል፣ አደረጃጀትና አሰራር ማሻሻልና የዕዉቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ለዉጥን ያመለክታል፡፡ | እውቀት፣ክህሎትና ፈጠራ |

# ደረጃ ሶስት

## 3. ስትራቴጂያዊ ግቦች

ስትራቴጂያዊ ግቦች ማለት የተመረጡ የትኩረት መስኮች ወደ ተጨባጭ ስራዎች በመመንዘር ስትራቴጂያዊ ውጤን የሚያስገኙ፣ ሊለኩ የሚችሉና የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ዉጤቶች የሚያሳኩ ቀጣይነት ያላቸዉ የማሻሻያ ክንዉኖች ናቸዉ፡፡

ስለሆነም በቢሮው አራት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች የተቀረፁ ሲሆን የእያንዳንዱን ትኩረት መስክ በሚያሳ መልኩ የተለያዩ ቁጥር ያላቸዉ ግቦች ተቀምጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት በእያንዳንዱ ስትራቴጂያዊ ውጤት ላይ እንደርሳለን የሚለውን ጥያቄ እንዲመልሱ ተደርገው ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

### 3.1. የትኩረት መስክ እና ስትራቴጂያዊ ግቦች

| ተ.ቁ | የትኩረትመስክ | ስትራቴጂያዊውጤት | ስትራቴጂያዊግብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ያደገ የኢንዱስትሪ ልማት | ያደገ ኢንዱስትሪ ተጠቃሚነት | ➢ ተደራሽነትን ማሳደግ፤<br>➢ የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ<br>➢ የኢንዱስትሪ ክላስተር ማልማት፣<br>➢ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ማሳደግ<br>➢ የአሠራር እና አደረጃጀት ሥርዓትን ማሻሻል፣<br>➢ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣<br>➢ ዘመናዊ መረጃ አጠቃቀም ስርዓትን ማሳደግ<br>➢ የኢንስፔክሽን እና ሬጉላቶሪ ስራዎችን ማጠናከር<br>➢ የባለሀብቶችን የኢንዱስትሪ ተሳትፎ ማሳደግ፣<br>➢ የበጀትአጠቃቀም ዉጤታማነት ማሳደግ<br>➢ የሰዉ ሀይል አቅም ማሳደግ፣<br>➢ የስራ አካባቢ ምቹነትን ማሻሻል |

| ተ.ቁ | የትኩረትመስክ | ስትራቴጂያዊውጤት | ስትራቴጂያዊግብ |
| --- | --- | --- | --- |
| 2. | የላቀ ኢንቨስትመንትን ልማት | ያደገ ኢንቨስትመንት ፍሰት | ➢ የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ<br>➢ ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>➢ የበጀት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>➢ ገቢን ማሳደግ<br>➢ የኢንቨስትመንት ልማት ማስፋፋት<br>➢ ክትትልና ድጋፍ ማሻሻል<br>➢ የአመራርና ሰራተኛ አቅምን ማሳደግ<br>➢ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት ማሻሻል<br>➢ ተቋማዊ አሠራር ማሳደግ |
| 3. | ስትራቴጂያዊ አጋርነት | የጎለበተ ቅንጅታዊ አሰራር ግንኙነት | ➢ የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ<br>➢ ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>➢ የበጀት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት<br>➢ የመረጃ ስርዓት ማጎልበት<br>➢ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሻሻል<br>➢ የሰራተኛን አቅም ማሳደግ |

| ተ.ቁ | የትኩረትመስክ | ስትራቴጂያዊውጤት | ስትራቴጂያዊግብ |
|---|---|---|---|
| 4. | የላቀ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም | ያደገ የማስፈጸም እና የመፈጸም አቅም | ➢ የተገልጋይ እርካታ ማሳደግ<br>➢ የሰዉ ሀይል አቅም ማሳደግ<br>➢ አሰራር እና አደረጃጀት ማሻሻል<br>➢ የበጀት አጠቃቀም ማሻሻል እና የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት<br>➢ ዘመናዊ የመረጃ አጠቃቀም ስርዓትን ማሳደግ<br>➢ የሥራ ባህልን ማዳበር<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ<br>➢ የስራ አካባቢ ምቹነትን ማሻሻል |

## 3.2. የቢሮ የተጠቃለለ ስትራቴጂያዊ ግቦች መግለጫያ

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
| የተገልጋይ | የተገልጋይ ዕርካታ ማሳደግ፣ | ተገልጋዩ ተቋሙ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ትኩረት ሰጥቶ በስታንዳርዱ መሰረት በመስራት የተገልጋይን እርካታ ማረጋገጥና የተገልጋዩን እርካታ ደረጃ በጥናትና መድረኮች በሚገኝ አስተያየት መሰረት ተገልጋዩ ያልረካባቸውን ክፍተቶች ለይቶ ማሻሻልን ይይዛል፤ | • የረኩ ተገልጋዮች |
| የፋይናንስ | የሃብት አጠቃቀም ዉጤታማነት ማሻሻል | ከመንግስት የሚመደብ የመደበኛና ካፒታል በጀት የፋይናንስ ህጉንና የፊዚካል እቅዶችን መሰረት አድርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣ ውጤታማ የንብረት አያያዝ ስርዓትን መዘርጋትና ውጤታማነቱን መከታተልን ያጠቃልላል። | • ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም |
| | ተቋማዊ ገቢ ማሳደግ | የኢንቨስትመት ፍቃድ በመስጠት ፣ ማደስ፣ትክ እና ለውጥ በማድረግ ገቢን ማሳደግ እና የተለያ ፕሮጀክቶችን ቀርያ ሀብት ማሰባሰብን ያካትታል። | • ያደገ ገቢ |
| የውስጥ አሰራር | የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማሳደግ | ከባላድርሻ አካላት ጋር በጋራ ማቀድ፣ አፈፃፀሙን መከታተልና ውጤታማ እንዲሆን የተለያ መድረኮችን ማዘጋጀትን ያካትታል። | • ያደገ የባለድርሻ ተሳትፎ<br>• ውጤታማ የሆነ ተሳትፎ |
| | የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ | ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለኢንዱስትሪ ልማት አመቺ የሆነ ቦታ በመከለል የማረቻ ሼዶችን በመገንባትና መሰረተ ልማትን በማሟላት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በማስተላለፍ ፣ መሠረተ ልማት በማሟላት ለባለሀብቶችና ለዲያስፖራዎች በማስተላለፍ ለልማት ተሳትፎ አመቺ ሁኔታ መፍጠርንና ክላስተሩን | • ለኢንዱስትሪ ልማት የተፈጠረ አመቺ ሁኔታ |

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
| | የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ማሳደግ | ነባር አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ማጠናከር፤አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በአዲስ ማቋቋም፤አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የካፒታል ሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዘመናዊ የሂሳብ አሠራር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤ለአምራች ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች እና ለፈፃሚ ባለሙያዎች የካይዘን ፍልስፍና፣የጥራትና የደረጃዎች ስልጠና መስጠት፤አነስተኛ እና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር እንዲያደርጉ ማድረግ | • የተስፋፋ ኢንዱስትሪ |
| | የኢንቨስትመንት ልማት ማስፋፋት | ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚሆኑ የሀብት አማራጮን በማጥናት ለልማታዊ ባለሃብቱ ማስተዋወቅ፣ በኢንቨስትመንት ዙሪያ የመጡ ለዉጦችንና ከዚሁ ጋር የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን በማጥናት የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ፣ ከሚመለከተዉ አካል ተዘጋጅቶ የቀረበ መሬት ለልማታዊ ባለሃብት ማስተዋወቅ፣ ያሉትን የኢንቨስትመንት ዕድሎች እና የሚሰጡ ማበረታቻዎችን ለልማታዊ፣ ባለሀብቶች በስፋት ማስተዋወቅ እና የተጠናከረ ፕሮሞሽን በማከናወን ኢንቨስትመንትን መሳብ፤ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በጥራትና በፍጥነት የመስጠት፣ | • ያደገ የኢንቨስትመንት ፍሰት |

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
| | የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ማሻሻል | ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት እና በድህረ ኢንቨስትመንት ደረጃ በኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚፈልጓቸውን መረጃዎች የመስጠት፣ ለባለሀብቱ የተሰጡ የተለያዩ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው አላማ ስለመዋላቸው የመከታተል፣ ለኢንዱስትሪና ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ቦታዎች ልማት ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በዕቅዳቸው መሠረት መተግበራቸውን የመከታተል፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤታማነትን ለሊያሻሽሉ የሚችሉ የክትትልና የድጋፍ ስራዎችን ያካትታል፡፡ | • የጎለበተ የድጋፍና ክትትል ስርዓት<br>• ውጤታማ የሆኑ ፕሮጀክቶች |
| | የአሰራር ስርዓት ማሻሻል | የህግ ማዕቀፎች/ደንብ፣ መመሪያ አዋጆች እንዲወጡ፣ በማሻሻልና እንዲሻሻሉ በማድረግ አደረጃጀቱ እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ ተፈትሾ እንዲስተካከል በማድረግና የመረጃ አቅርቦትና ተደራሽነት ማሳደግን ያካተተ ይሆናል፡፡ | • የተቀላጠፈ የአሰራር ስርዓት‹ |
| | የዘርፍ ብዙ ጉዳዮች ዉጤታማነትን ማሻሻል፣ | በተቋሙ የሚሠሩ ስራዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ያማከለ መሆኑን ማረጋገጥን፣ የችግኝ ተከላ፣ ለተለያዩ አቅመደካሞች የሚደረግ ድጋፍ እና ሌሎችን ያካትታል፡፡ | • ምላሽ ያገኙ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች፣ |
| የመማማርና እድገት | የሰዉ ኃይል አያያዝና ብቃት ማሻሻል፣ | የዘርፉን ልማት ሊደግፍ በሚችል አግባብ የሙያ ብቃትንና አመላካከትን የሚያሻሽሉና የለውጥ ፕሮግራሞችን መሰረት ያደረገ ለሰራተኛው የአጭር ጊዜ ስልጠና በመስጠት፣ የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን በማመቻቸት የሰራተኛውን የእውቀት፣ የክህሎት አቅሙን የማሻሻል፣ ለአዲስ ሰራተኞች የሥራ ትዉዉቅ ስልጠና መሰረት አድርጎ የሚከናዉኑ ተግባራትንና የማበረታቻ ስርዓትን ያካትታል፡፡ | • አቅማቸዉ የጎለበተ አመራሮችና ሰራተኞች፣ |

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
| | የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል፣ | ብሮድ ባንድ ኢንተርኔት፣ጂፒኤስ፣እስካነር፣ቪዲኦ ካሜራ ፣የመረጃ ኔትወርኪንግ እና ሌሎች አቅርቦቶችን ማሳደግ፣ ስለ መረጃ ጠቀሜታ ለፈፃሚ አካላት በቂ ግንዛቤ መፍጠር፤ የሴክተሩን መረጃዎች መለየት፣ መሰብሰብ፣መተንተንና ጥቅም ላይ ማዋል፤ የተቋሙን የመረጃ ቋት ማዘጋጀትና መረጃዎችን ማስገባት፤ የመረጃ መረብ በቢሮው መክፈትና ወቅታዊ መረጃዎችን ማስተላለፍና ግብረ-መልስ መቀበል፤የተቋሙን የ IT ክህሎት ማሳደግን ያካትታል፡፡ | • ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ<br>• ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት |

### 3.3. የቢሮ የተጠቃለለ ስትራቴጂያዊ ግቦች


| ተ/ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | ክብደት | መለኪያ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተገልጋይ ዕርካታ ማሳደግ፣ | 2.5 | በመቶኛ |
| 2 | የሃብት አጠቃቀም ዉጤታማነት ማሻሻል | 2.5 | በመቶኛ |
| 3 | ተቋማዊ ገቢ ማሳደግ | 2.5 | በመቶኛ |
| 4 | የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማሳደግ | 2.5 | በመቶኛ |
| 5 | የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ | 20 | በመቶኛ |
| 6 | የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ማሳደግ | 20 | በመቶኛ |
| 7 | የኢንቨስትመንት ልማት ማስፋፋት | 27 | በመቶኛ |
| 8 | የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ማሻሻል | 13 | በመቶኛ |
| 9 | የዘርፍ ብዙ ጉዳዮች ዉጤታማነትን ማሻሻል፣ | 1 | በመቶኛ |
| 10 | የሰዉ ኃይል አያያዝና ብቃት ማሻሻል፣ | 2 | በመቶኛ |
| 11 | የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል፣ | 3 | በመቶኛ |
| 12 | የአሰራር ስርዓት ማሻሻል | 4 | በመቶኛ |
| | አጠቃላይ ድምር | **100** | |

# ደረጃ አራት

## 4. ስትራቴጂያዊ ማፕ

ስትራቴጂያዊ ማፕ በተለያዩ ዕይታዎች ስር የሚቀረጹ ስትራቴጂያዊ ግቦች በምክንያትና ውጤት ተሳስረው እንዴት ተጨማሪ እሴት በመፍጠር ስትራቴጂያዊ ውጤትን እንደሚያሳኩ የምንመለክትበት ምስል ነው፡፡ ይህ ማፕ የግቦች ተመጋጋቢነት የሚታይበትና ስትራቴጂው በአጭሩ የሚተረክበት ስዕላዊ መግለጫ ሲሆን፣ ስትራቴጂውን በትክክል ለመግለጽና ለማስገንዘብ ብሎም ሁሉም ፈጻሚዎች የራሳቸው እንዲያደርጉት የሚያግዝ መሣሪያ ነው፡፡

በተቋሙ ለተለዩት አራት የትኩረት መስኮች ለእያንዳንዳቸዉ ስትራቴጂያዊ ማፕ በተናጠል የተዘጋጀ ሲሆን፣ በመቀጠልም ለሶስት የትኩረት መስኮች የተዘጋጁ ስትራቴጂያዊ ግቦችን በማዋሃድና በማዋዋጥ የተቋሙ የተጠቃለለ ስትራቴጂያዊ ማፕ ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡


ዕይታ
የተጠቃለለ ስትራቴጂያዊ ማፕ
ተገልጋይ
የተገልጋይ ዕርካታ ማሳደግ፤
በጀት/ፋይናንስ
ተቋማዊ ገቢ ማሳደግ
የሃብት አጠቃቀም ዉጤታማነት ማሻሻል
የውስጥ አሠራር
የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ
በኢንቨስትመንት ልማት ማስፋፋት
የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ማሳደግ
የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማሳደግ
የዘርፍ ብዙ ጉዳዮች ዉጤታማነትን ማሻሻል፤
የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ማሻሻል
መማማርና ዕድገት
የአሰራር ስርዓት ማሻሻል
የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል፤
የሰዉ ኃይል አያያዝና ብቃት ማሻሻል፤

## 4.1. የተቋሙ የተጠቃለሉ ስትራቴጂያዊ ግቦች

ለሁለቱ የትኩረት መስኮች የተዘጋጁ ዝርዝር ስትራቴጂያዊ ግቦችን በማዋሃድና በማዋዋጥ የተቋሙ የተጠቃለሉ ስትራቴጂያዊ ግቦች በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

| እይታ | ተ/ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች |
|---|---|---|
| ተገልጋይ | 1 | የተገልጋይ ዕርካታ ማሳደግ፣ |
| የፋይናንስ/ የበጀት | 2 | የሃብት አጠቃቀም ዉጤታማነት ማሻሻል |
| | 3 | ተቋማዊ ገቢ ማሳደግ |
| የውስጥ አሰራር | 4 | የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማሳደግ |
| | 5 | የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ |
| | 6 | የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ማሳደግ |
| | 7 | የኢንቨስትመንት ልማት ማስፋፋት |
| | 8 | የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ማሻሻል |
| | 9 | የዘርፍ ብዙ ጉዳዮች ዉጤታማነትን ማሻሻል፣ |
| መማማርና እድገት | 10 | የሰዉ ኃይል አያያዝና ብቃት ማሻሻል፣ |
| | 11 | የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል፣ |
| | 12 | የአሰራር ስርዓት ማሻሻል |
| | | አጠቃላይ ድምር |

# ደረጃ አምስት

## 5. ስትራቴጂያዊ መለኪያዎችና ዒላማዎች

### 5.1. ስትራቴጂያዊ መለኪያዎች

የአፈጻጸም መለኪያ በተጠቃለለው የስትራቴጂ ማፕ የተቀመጡ ግቦችን የስኬት ደረጃ (ውጤት) ለመመዘን የሚያስችል መሣሪያ ነው:: በመሆኑም የአፈጻጸም መለኪያዎች፣

- የተቋሙን ስትራቴጂያዊግቦች አፈጻጸም ለመከታተል የሚያስችሉ፣
- በስትራቴጂ ዘመኑ በታቀደውናእየተፈጸመ ባለው መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳዩ፣
- ተቋማዊ ውጤታማነትናቅልጥፍናበግልጽ የሚመለከትባቸው የአፈጻጸም አመራር እምብርት ናቸው::

ግቦች መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ በቅድሚያ ግቦቹ ስለመፈፀማቸው ማረጋገጫ/ማሳያ የሚሆን የአፈፃፀም መግለጫ ሊኖር ይገባል፡፡ ስለሆነም ይህ ማረጋገጫ የአፈፃፀም አመልካች (Performance Indicator) ይባላል፡፡ የአፈፃፀም መለኪያዎች (Performance Measures) ደግሞ የተገኘውን የግብ ውጤት የስኬት ደረጃ ለማወቅ የምንችልበት መሣሪያ ነው፡፡ በዕቅድ ዘመኑ መፈፀም አለበት ተብሎ የሚቀመጠው የግብ ውጤት የስኬት ደረጃ ደግሞ ዒላማ (Target) መለካት የሚቻል ሲሆን ዒላማዎችም በቁጥር፣ በጥምርታ እና በመቶኛ ሊገለጽ ይችላል፡፡ የተቋሙ የአፈፃፀም መለኪያዎችና ዒላማዎች በዝርዝር ቀጥሎ ባሉት ሠንጠረዦች ተመልክተዋል፡፡

| ተ/ቁ | ዕይታዎች | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | | መለኪያ | ክብደት በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕይታ | ግብ | | | |
| 1 | ተገልጋይ | የተገልጋይ ዕርካታ ማሳደግ፣ | 2.5 | 2.5 | የረኩ ተገልጋዮች በመቶኛ | 2.5 | |
| 2. | የፋይናንስ/ የበጀት | የሃብት አጠቃቀም ዉጤታማነት ማሻሻል | 5 | 2.5 | የበጀት አጠቃቀም ዉጤታማነት በመቶኛ | 2.5 | |
| | | ተቋማዊ ገቢ ማሳደግ | | 2.5 | ያደገ ገቢ በብር | 2.5 | |
| 3. | የውስጥ አሰራር | የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማሳደግ | 83.5 | 2.5 | ያደገ የባለድርሻ ተሳትፎ በቁጥር | 1.5 | |
| | | | | | ውጤታማ የሆነ ተሳትፎ በመቶኛ | 1 | |
| | | የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ | | 20 | የተከለለ የኢንዱስትሪ መሬት በሄ/ር | 8 | |
| | | | | | የለማ የኢንዱስትሪ ክላስተር በሄክታ | 6 | |
| | | | | | የተላለፈ የኢንዱስትሪ ክላስተር በቁጥር | 6 | |
| | | የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ማሳደግ | | 20 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የኢኮኖሚ ድርሻ በመቶኛ | 6 | |
| | | | | | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የእድገት ምጣኔ በመቶኛ | 6 | |
| | | | | | ያደገ የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም በመቶኛ | 5 | |
| | | | | | በአዲስ የተቋቋሙ አምራች ኢንዱስትሪዎች በቁጥር | 3 | |
| | | የኢንቨስትመንት ልማት ማስፋፋት | | 27 | የተጠና ሰነድ በቁጥር | 8 | |
| | | | | | የተዘጋጀ መሬት በሄ/ር | 7 | |
| | | | | | የተሰራ ፕሮሞሽን በመቶኛ | 10 | |
| | | | | | ፈቃድ የወሰዱ ባለሃብቶች በቁጥር | 2 | |
| | | የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ማሻሻል | | 13 | ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶች | 5 | |
| | | | | | ውጤታማ የሆኑ ፕሮጀክቶች በመቶኛ | 5 | |
| | | | | | ወደ ምርት የገቡ ፕሮጀክቶች በቁጥር | 3 | |
| | | የዘርፍ ብዙ ጉዳዮች ዉጤታማነትን ማሻሻል፣ | | 1 | ምላሽ ያገኙ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በመቶኛ | 1 | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | መማማር ና እድገት | የሰዉ ኃይል አያያዝና ብቃት ማሻሻል፣ | 9 | 2 | የተሟላ የሰዉሀይል በመቶኛ | 1 | |
| | | | | | በረጅም እና በአጭር ጊዜ የተሰጠ ስልጠና በቁጥር | 1 | |
| | | የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል፣ | | 3 | ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ ሽፋን በመቶኛ | 2 | |
| | | | | | የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በመቶኛ | 1 | |
| | | የአሰራር ስርዓት ማሻሻል | | 4 | የተሻሻለ አሰራር ስርዓት በመቶኛ | 2 | |
| | | | | | የተሻሻለ አደረጃጀት በሰነድ | 2 | |
| | | አጠቃላይ ድምር | 100 | 100 | | 100 | |

## 5.2. ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ መለኪያዎች እና ዒላማዎች የሁለት ዓመት ተደራሽ

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት | መለኪያ | ክብደት | መነሻ (2012) | የ5 ዓመት ተደራሽ | ዒላማዎች 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተገልጋይ | የተገልጋይ ዕርካታ ማሳደግ፣ | 2.5 | የረኩ ተገልጋዮች በመቶኛ | 2.5 | 74 | 90 | 82 | 90 |
| የፋይናንስ/ የበጀት | የሃብት አጠቃቀም ዉጤታማነት ማሻሻል | 2.5 | የበጀት አጠቃቀም ዉጤታማነት በመቶኛ | 2.5 | 83 | 100 | 100 | 100 |
| | ተቋማዊ ገቢ ማሳደግ | 2.5 | ያደገ ገቢ በብር | 2.5 | 1,514,006 | 1,904,756 | 1,732,656 | 1,904,756 |
| የውስጥ አሰራር | የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማሳደግ | 2.5 | ያደገ የባለድርሻ ተሳትፎ በቁጥር | 1.5 | -- | 15 | 15 | 15 |
| | | | ውጤታማ የሆነ ተሳትፎ በመቶኛ | 1 | -- | 80 | 70 | 80 |
| | የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ | 20 | የተከለለ የኢንዱስትሪ መሬት በሄ/ር | 8 | 100 | 400 | 350 | 400 |
| | | | የለማ የኢንዱስትሪ ክላስተር በሄክታ | 6 | 0 | 250 | 250 | 250 |
| | | | የተላለፈ የኢንዱስትሪ ክላስተር በቁጥር | 6 | 0 | 1 | | 1 |
| | የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ማሳደግ | 20 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የኢኮኖሚ ድርሻ በመቶኛ | 6 | 0.81 | 5.21 | 29.2 | 29.2 |
| | | | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የእድገት ምጣኔ በመቶኛ | 6 | 4.9 | 9.2 | 9.2 | 9.2 |
| | | | ያደገ የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም በመቶኛ | 5 | 50 | 61 | 59 | 61 |
| | | | በአዲስ የተቋቋሙ አምራች ኢንዱስትሪዎች በቁጥር | 3 | 52 | 110 | 23 | 24 |
| | የኢንቨስትመንት ልማት | 27 | የተጠና ሰነድ በቁጥር | 8 | 1 | 4 | 3 | 4 |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት | መለኪያ | ክብደት | መነሻ (2012) | የ5 ዓመት ተደራሽ | ዒላማዎች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 2016 | 2017 |
| | ማስፋፋት | | የተዘጋጀ መሬት በሄ/ር | 7 | 35,240 | 101,241 | 79,240 | 101,241 |
| | | | የተሰራ ፕሮሞሽን በቁጥር | 10 | 35 | 205 | 135 | 205 |
| | | | ፈቃድ የወሰዱ ባለሃብቶች በቁጥር | 2 | 3977 | 4901 | 4586 | 4901 |
| | የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ማሻሻል | 13 | ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶች | 5 | 332 | 1052 | 957 | 1052 |
| | | | ውጤታማ የሆኑ ፕሮጀክቶች በመቶኛ | 5 | 126 | 570 | 450 | 570 |
| | | | ወደ ምርት የገቡ ፕሮጀክቶች በቁጥር | 3 | -- | 110 | 100 | 110 |
| | የዘርፍ ብዙ ጉዳዮች ዉጤታማነትን ማሻሻል፣ | 1 | ምላሽ ያገኙ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በመቶኛ | 1 | -- | 100 | 90 | 100 |
| መማማር ና እድገት | የሰዉ ኃይል አያያዝና ብቃት ማሻሻል፣ | 2 | የተሟላ የሰዉ ሀይል በመቶኛ | 1 | 22 | 70 | 50 | 70 |
| | | | በረጅም እና በአጭር ጊዜ የተሰጠ ስልጠና በቁጥር | 1 | -- | 200 | 100 | 200 |
| | የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል፣ | 3 | ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ ሽፋን በመቶኛ | 2 | 50 | 75 | 52 | 75 |
| | | | የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በመቶኛ | 1 | 50 | 58 | 56 | 58 |
| | የአሰራር ስርዓት ማሻሻል | 4 | የተሻሻለ አሰራር ስርዓት በመቶኛ | 2 | 65 | 78 | 75 | 78 |
| | | | የተሻሻለ አደረጃጀት በሰነድ | 2 | | 12 | 8 | 12 |

### 5.3. የግብ ማሳኪያ ዋና ዋና ተግባራት (2016-2017)

| ተ/ቁ | ስትራቴጂክ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | ግብ ክብደት | መለኪያ | መነሻ | የሁለት ዓመ ቱ ዒላማ | የሚደረስበት ትንበያ በበጀትዓመቱ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 2016 | 2017 |
| ግብ.1 | የተገልጋይ ዕርካታ ማሳደግ | 2.5 | | | | | |
| 1.1 | የተገልጋይ ዕርካታን ለማሳደግ የዳሰሳ ጥናቶችን ማድረግ | | በሰነድ | 0 | 2 | 1 | 2 |
| 1.2 | የተሰሩትን የዳሰሳ ጥናቶች መሰረት በማድረግ የአሰራር ስርዓት ለዉጥ ማድረግ | | በመቶኛ | 74 | 90 | 82 | 90 |
| ግብ.2 | የሃብት አጠቃቀም ዉጤታማነት ማሻሻል | 2.5 | | | | | |
| 2.1 | የበጀት አጠቃቀም የሚያሻሽሉ ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ | | በመቶኛ | 83 | 100 | 100 | 100 |
| 1.2 | የግዥና የንብረት አስተዳደር ስርዓትን ማዘመኛ ስራዎችን መስራት | | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 |
| ግብ.3 | ተቋማዊ ገቢ ማሳደግ | 2.5 | | | | | |
| 3.1 | የተለያዩ ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀት ገቢን ማሳደግ | | ብር በሚ. | **0** | 10 | 5 | 10 |
| 3.2 | በኢንቨስትመንት ፈቃድ አገልግሎት ክፊያ ገቢ ማሳደግ | | ብር በሚ. | 1,514,006 | 1,904,756 | 1,732,656 | 1,904,756 |
| ግብ.4 | የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማሳደግ | 10 | | | | | |
| 4.1 | የመግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት ባለድርሻ አካላት ጋር መፈራረም | | በቁጥር | 0 | 15 | 15 | 15 |
| 4.2 | የመግባቢያ ሰነዱን አፈፃፀም ውጤታማነት በጋራ መገምገም | | በመቶኛ | 0 | 80 | 70 | 80 |
| 4.3 | የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የዉይይት መድረኮችን ማድረግ | | በመድረክ | 5 | 16 | 8 | 8 |
| ግብ.5 | የኢንዱስትሪ ልማት ማሳደግ | 20 | | | | | |
| 5.1 | በ4ቱም ከተሞች ኢንዱስትሪ ክላስተር የሚውል መሬት መከለል | | በሄ/ር | | 250 | 100 | 150 |
| 5.2 | በ4ቱም ከተሞች ለኢንዱስትሪ ክላስተር እንዲለማ ማድረግ | | በሄ/ር | | 150 | 100 | 50 |
| 5.3 | ለኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ የሚሆን መሬት ማዘጋጀት | | በሄ/ር | 100 | 600 | 250 | 300 |

| ተ/ቁ | ስትራቴጂክ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | | ግብ ክብደት | መለኪያ | መነሻ | የሁለት ዓመ ቱ ዒላማ | የሚደረስበት ትንበያ በበጀትዓመቱ 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብ.6 | የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ማሳደግ | | 20 | | | | | |
| 6.1 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የኢኮኖሚ ድርሻ ማሳደግ | | | በመቶኛ | 0.81 | 5.21 | 29.2 | 29.2 |
| 6.2 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የእድገት ምጣኔ ማሳደግ | | | በመቶኛ | 4.9 | 9.2 | 9.2 | 9.2 |
| 6.3 | የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም ማሳደግ | | | በመቶኛ | 50 | 61 | 59 | 61 |
| 6.4 | አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም | | | በቁጥር | 52 | 110 | 23 | 24 |
| ግብ.7 | የኢንቨስትመንት ልማት ማስፋፋት | | 27 | | | | | |
| 7.1 | አዲስ የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጭ እና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ተፅዕኖ ጥናት ማካሄድ | ሀብት | | በሰነድ | 1 | 4 | 3 | 4 |
| | | ተጽዕኖ | | በሰነድ | | 3 | 2 | 3 |
| 7.2 | ለተጠኑ አዲስ የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጮች ፕሮፋል ማዘጋጀት | | | በቁጥር | | 28 | 22 | 28 |
| 7.3 | ለግብርና ኢንቨ/አገልግሎት አገልግሎት የሚዉል መሬት እንዲተላለፍ ከሚመለከታቸው አካት ምቹ ሁነታ ይፈጥራል፣ | | | በሄ/ር | 35,241 | 101,241 | 79,240 | 101,241 |
| 7.4 | ለከተማ ኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚዉል መሬት ከሚመለከታቸዉ አካላት በመረከብ ለፕሮሞሽን ምቹ ማድረግ፣ | | | ካ/ሜ | 1,207,151 | 1,813,202 | 1,675,843 | 1,813,202 |
| 7.5 | የክልሉልን የኢንቨ/ት ሀብት አማራጮች በማስተዋወቅ ባለሀብቶችን መሳብ | | | በቁጥር | 35 | 205 | 135 | 205 |
| 7.6 | መስፈርቶችን አሟልተዉ ለሚቀርቡ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት | | | በቁጥር | 3,977 | 4,901 | 4,586 | 4,901 |
| ግብ.8 | የኢንዱስትሪና ኢንቨሰትመንት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ማሻሻል | | 13 | | | | | |
| 8.1 | የኢንቨስትምንት ፕሮጀክቶች አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ወደ ስራ ማስገባት፣ | | | በቁጥር | 458 | 1458 | 1306 | 1458 |
| 8.2 | የኢንዱስትሪና የኢንቨስትምንት ፕሮጀክቶች ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ መውሰድ | | | በቁጥር | 126 | 570 | 450 | 570 |
| 8.3 | ለማንፋክቸሪንግ ፕሮጀክቶች አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣ ወደ ምርት እንዲገቡ ክትትል ማድረግ፣ | | | | -- | 110 | 100 | 110 |
| 8.4 | በኢንዱስትሪውና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ክትትል በማድረግ የተፈጠረ የስራ ዕድል ማረጋገጥ | | በቁጥር | ቋሚ | 4,153 | 4,354 | 4,153 | 4,354 |
| | | | | ጊዜዊ | 18,714 | 14,396 | 14,195 | 14,396 |

| ተ/ቁ | ስትራቴጂክ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | ግብ ክብደ ት | መለኪያ | መነሻ | የሁለት ዓመ ቱ ዒላማ | የሚደረስበት ትንበያ በበጀትዓመቱ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 2016 | 2017 |
| ግብ.9 | የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ዉጤታማነትን ማሻሻል | 6 | | | | | |
| 9.1 | በተቋሙ የሚሠሩ ስራዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ያማከለ መሆኑን ማረጋገጥንና ድጋፍ ማድረግ | | በመቶኛ | -- | 100 | 90 | 100 |
| ግብ.10 | የሰዉ ኃይል አያያዝና ብቃትማሻሻል፣ | 6 | | | | | |
| 10.1 | ተቋሙን በሰው ኃይል ማሟላት | | በቁጥር | 22 | 70 | 50 | 70 |
| 10.2 | በረጅም እና በአጭር ጊዜ የተሰጠ ስልጠና መስጠት | | በቁጥር | -- | 200 | 100 | 200 |
| ግብ.11 | የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል፣ | 7 | | | | | |
| 11.1 | ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ ማደራጀትና ተደራሽ ማድረግ | | በመቶኛ | 50 | 75 | 52 | 75 |
| 11.2 | በቢሮው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግ | | በመቶኛ | 50 | 58 | 56 | 58 |
| ግብ.12 | የአሰራር ስርዓትማሻሻል | 2 | | | | | |
| 12.1 | የቋሙን አደራጃጀትና ሌሎች የህግ ማዕቀፎችና መንዋሎችን ማሻሻል | | በሰነድ | -- | 12 | 8 | 12 |
| 12.2 | የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እርምጃዎችን በመውሰድ ጥራ ያለው አገልግሎት መስጠት | | በመቶኛ | 65 | 78 | 75 | 78 |

## 5.4. ተቋማዊ ዒላማዎች መግለጫ እና የአፈፃፀም ደረጃ መነሻ ሀሳብ

የዒላማዎች መግለጫ የአፈፃፀም ደረጃ መነሻ ሀሳብ (threshold) ተቋማችን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማጠናቀቂያ ወቅት ላይ እንደመገኘቱ ሊደረስባቸው የሚገቡ በጥረት ተደራሽ ግቦች ሙሉ በሙሉ ≥70% ማሳካት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም የዒላማ አፈፃፀም ደረጃ ማለትም ቀይ የዒላማውን < 51% በታች የማሳካት ተግባር ከተከናወነ በየደረጃው የሚገኙ የተቋሙ አመራሮችና ሰራተኞች ቀጣይ አፈጻጸማቸውን እንዲያሻሽሉ አፋጣኝ እርምጃዎችን መዉሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

51%≤% ን-<70% ያለው የአፈፃፀም ደረጃ ቢጫ የሚባለው ውስጥ የሚወድቅ ሲሆን ይህም የታለመውን ዒላማ በቁርጠኝነት ለማሳካት ተጨባጭና ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ከአመራሮችና ከሰራተኛው የሚጠበቅ ሲሆን የዒላማው ≥ 70% እና ከዚያ በላይ የአፈፃፀም ደረጃ ላይ ከደረሰን አረንጓዴ ቀለም ላይ ሲሆን ይህም በየደረጃው የተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግቦች የወረደላቸው ዳይሬክቶሬቶች ይህ ግብና ከግቡ ጋር ተዛማችነት ያላቸው ተግባራት የአመራሮችና የሠራተኛው ሥራ ባህል መገለጫ ሆነው ይቀጥሉና ለተገኘው መሳካት በየደረጃው የሚገኙ አካላት በተቋም፣ በአመራር እና በሠራተኛ ደረጃ የሚገባቸውን የማትጊያ እና የማበረታቻ ሽልማት በተዘጋጀው የማስፈጸሚያ ሰነድ መሰረት የሚፈፀምበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸው ይደረጋል፡፡

ይህ የአፈፃፀም ደረጃ በየአመቱ የሚሠላ ሆኖ በስሌቱም መሰረት የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች በተቀመጡት የአፈፃፀም መገምገሚያ ነጥቦች መሰረት በማድረግና የማስተካከያ/ክለሳ ሥራዎች እንዲሠሩ በቁልፍ ግብዓትነት ያገለግላል፡፡

| ቀይ | ቢጫ | አረንጓዴ |
|---|---|---|
| < 51% | 51%≥ ን < 70% | ≥ 70% |